# ክፍል ሦስት

# የእረኛው ልብ

## ምዕራፍ 36

# ልብህ የአገልግሎትህ ማዕከል ነው

የሰው ልብ በሰውነታችን መሀከል ላይ የሚገኝ የርጭት ማሽን ነው፡፡ ልባችን በዋነኛነት ሥራው መርጨት እንደሆነ እናውቃለን፡፡ ነገር ግን ደግሞ ልብ የሰው አካል ማዕከል እንደሆነም እናውቃለን፡፡ ‹‹ልብ›› የሚለው ቃል የመጣው ላባብ (labab) ከሚል የዕብራይስጥ ቃል ሲሆን ልብ የሰውነት ማዕከል መሆኑ በትኩረት ያሳያል፡፡

መጽሀፍ ቅዱስ በልብ የደም መርጨት ተግባር ይልቅ የሰውነት ውስጠኛው ማዕከል በመሆኑ ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ ለዚህ ነው ‹‹ልብ›› የሚለው ቃል ‹‹የባህር ልብ›› ፣ ‹‹የሰማያት ልብ›› ፣ ‹‹ የዛፍ ልብ›› እና ‹‹ የምድር ልብ›› በሚሉ አገላለጾች ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለው፡፡

## የአገልግሎትህ ማዕከል ምንድነው?

1. የአንድ ነገር የተመረጠ ክፍል
2. የአንድ ዕቃ በጣም ጠቃሚ የሆነ አካል
3. የአንድ ሀሳብ ወይም ልምድ በጣም ጠቃሚ ክፍል
4. ትኩረትና ፍላጎት ያረፈበት ዕቃ
5. የአንድ ነገር ማዕከል የዚያን ነገር መሰረት ያመለክታል
6. አንድ የተለየ ነገር በትኩረት የሚከናወንበት ቦታ
7. የወታደር ወይም የባህር ኃይል ቡድን ማዕከል
8. የህይወትህ መንፈሳዊ የትኩረት ማዕከል
9. በዙሪያው ብዙ ጉዳዮች የሚያጠነጥኑበት የትኩረት ማዕከል

## 10. ነገሮች በዙሪያው የሚሽከረከሩበት ኑክለስ (እምብርት)

ለዚህ ነው ልብ እጅግ አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት። መሠረት የሚጠበቀውን ውጤት እንደሚወስን ለሁላችንም ግልጽ ነው። ለዚህም ነው የአንድ ሰው አገልግሎት በልቡ ባለው ነገር ላይ የሚወሰነው።

በሰብአዊ ተፈጥሮአችን ምክንያት ልብን ችላ ብለን ግምገማችንን በውጫው ነገር ላይ እናደርጋለን። ነገር ግን ውጫዊ ገጽታ ስውር ከሆነው የሰው ልብ አንጻር ስለ አንድ ሰው የሚሰጠው መረጃ አነስተኛ ነው። የሰው ሁሉ የህይወቱና አገልግሎቱ ማዕከል ልቡ ነው። አንድ ጉዳይ የሚመነጨው ከአንድ ነገር ማዕከል ነው። ለዚህ ነው የብዙ አገሮች ዋና ከተሞች በአገሪቱ መካከለኛ ቦታዎች የሚገኙት። ለምሳሌ ሮም፣ ማድሪድ፣ ቶክዮ፣ ቦጎታ፣ ብራዚል እና አቡጃ ከሞላ ጎደል በአገሮቻቸው መካከል ላይ የሚገኙ ከተሞች ናቸው። የአንድ አገር ርቀት የሚለካውም ከመካከለኛ ሥፍራው ነው። በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አንድ ነገር በልቡ ዙሪያ የሚሽከረከር ስለመሆኑ መገለጥን ይሰጡናል።

1. የባህር ልብ። ይህ ስለ ባህር ውስጠኛና ጥልቅ ክፍል የሚናገር ነው

"በአፍንጫህ እስትንፋስ ውኆች ተከመሩ፥ ፈሳሾቹም እንደ ክምር ቆሙ ጥልቆችም በባሕር ውስጥ ረጋ ።"

ዘጸአት 15:8

2. የሰማይ መካከል። የሰማይን ውስጠኛ፣ ምስጢራዊ እና የቅርብ ክፍል የሚያመለክት ነው።

"እናንተም ቀርባችሁ ከተራራው በታች ቆማችሁ ነበር እስከ ሰማይም መካከል ድረስ እሳት በተራራው ላይ ይነድድ ነበር ጨለማና ደመና ድቅድቅ ጨለማም ነበረ።"

ዘዳግም 4:11

3. የዛፍ መካከል። የዛፍን እምብርትና መካከለኛ ሥፍራ የሚያመለክት ነው።

"ኢዮአብም። እኔ ከአንተ ጋር እንዲህ አዘገይ ዘንድ አልችልም ብሎ ሦስት ጦሮች በእጁ ወሰደ፥ አቤሴሎምም ገና በዛፍ ላይ ተንጠልጥሎ ሕያው ሳለ በልቡ ላይ ተከላቸው።"

2ኛ ሳሙኤል 18፡14

4. የምድር ልብ። የምድርን ውስጣዊና ጥልቅ ክፍል ያመለክታል።

"ዮናስ በዓሣ አንባሪ ሆድ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ነበረ፥ እንዲሁ የሰው ልጅ በምድር ልብ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ይኖራል።"

ማቴዎስ 12፡40

5. የህይወትህ ልብ የህይወትህ ማዕከል ነው።

"አእምሮንም ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል።"

ፊልጵስዩስ 4፡7

ምናልባት አሁን መጽሐፍ ቅዱስ ለምን ልባችንን አጥብቀን እንድንጠብቅ እንደሚያስምረን ገብቶህል ብዬ አስባለሁ። ልብ የአንድ ነገር በጣም አስፈላጊ ክፍል ከሆነ በከፍተኛ ቅንአት መጠበቁ የሚያስገርም አይደለም። ‹‹አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ፥ የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነውና።›› (ምሳሌ 4፡23)

## ምዕራፍ 37

# ከሰው የተፈጥሮ ልብ ጋር በማወዳደር ስለመንፈሳዊ ልብ መረዳት

1. የሰው የተፈጥሮ ልብ የሚገኘው በሁለቱ ጡቶቹ መካከል ነው። ይህ የሚያሳየን የሰው መንፈሳዊ ልብ በሰውዬው አስተሳሰብ፣ ቃለት፣ ተግባር እና አገልግሎት መካከል እንደሆነ ነው። የሰው ልብ የአገልግሎቱ ዋና መሰረት ነው። ለዚህ ነው ልብ በጣም አስፈላጊ የሚሆነው። ማንኛውም ሰው የሚያከናውነውን ነገር በልቡ ላይ የተመሠረተ ነው። የምትሆነው ሁሉ በልብ ላይ የተመሠረተ ነው።

2. የሰው የተፈጥሮ ልብ መጠኑ የእጁን ጭብጥ ያህል ነው። በሌላ አባባል ልብህ የሚያክለው የእጅህን ያህል ነው። ይህ ምን ማለት ነው? ይህ የሚያሳየው የእጅህ ሥራ መጠኑ የልብህን ያህል እንደሚሆን ነው። ልብህ ትልቅ በሆነ መጠን እጅህም ትልቅ ይሆናል። ልብህ ተለቅ ሲል በእጆችህ ተለቅ ያለ ሥራ ለመሥራት ትችላለህ። ታላላቅ ነገሮችን ማከናወን ትችል ዘንድ እግዚአብሔር በልብህ እንዲሰራ የምትፈቅድበት ጊዜው አሁን ነው። የአንድ ሰው አገልግሎት ስፋት የሚወሰነው በልቡ ስፋት ነው።

3. የሰው የተፈጥሮ ልብ ንጥረ ነገሮችን ሁሉ የያዘ ደም አለው። ንጥረነገሮቹ የሚገኙት ከምትመገበው ነገር ነው። ይህም ወደ ውስጥህ የምታስገባው ነገር በልብህ ላይ ተጽዕኖ እንዳለው ያሳያል። የመንፈሳዊ ልብህ ይዘት በምትሰማውና በምትቀበለው ነገር የተገነባ ነው። ብዙ ነገሮች ለጥቂት ጊዜ በአዕምሮህ ከቆዩ በኋላ ወደ ልብህ ይገባሉ። ክፉ ነገሮች ወደ ልብህ እንዳይገቡ መከላከል አለብህ።

4. የሰው የተፈጥሮ ልብ የሚሰራው ደም በመቀበልና በመስጠት ነው። ይህ እውነታ ልብ ለሰው ህይወት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ያስገነዝበናል። ወደ ልብ የገባው ያው ደም

ነው ወደ ሌላው የሰውነት ክፍል የሚረጨው። አንድ ሰው ደም ወደ ልቡ ይቀበላል ከዚያም ንጹህና የተጣራ ደም ለሌላው የሰውነት ክፍል ያሰራጫል። ይህ ማለት ወደ ውጭ የምታወጣው ወደ ልብህ እንዲገባ ከፈቀድከው ነገር ነው።

5. **የሰው የተፈጥሮ ልብ በርቀት ላሉ የሰውነት ክፍሎች ሁሉ ደም ያሰራጫል።** ከዚህም መንፈሳዊ ልብ ጥልቅ የሆነውንና አነስተኛ የሚባሉትን የህይወትህ ክፍሎች ላይ ተጽዕኖ እንዳለው እንረዳለን። እያንዳንዱ የህይወትህ ጥቃቅን ክፍል በልብህ ባለው ነገር ተጽዕኖ ሥር ነው። ያንተ በሆነው ነገር ሁሉ ላይ ተጽዕኖ የማድረግ አቅም ስላለው ልብ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው።

6. **የሰው የተፈጥሮ ልብ ኦክሲጅን የያዘ ደም በመርጨት ለተቀረው የሰውነት ክፍል ህይወት ይሰጣል።** ይህም የሚያሳየው የሰው ልብ ህይወትን፣ ደስታንና ሠላምን የሚሰጥ መሆኑን ነው። የአገልግሎትህ ህይወት ሰጪ ክፍል ልብህ ነው።

7. **የሰው የተፈጥሮ ልብ በሚበከልበት ጊዜ መላውን የሰውነት ክፍል የሚበክል ደም ይሰራጫል።** በተመሳሳይ መልኩ መንፈሳዊ ልብ በየትኛውም አይነት ክፋት ሲበከል ቆሻሻው ወደ ተቀረው የሰውነት ክፍል ይሰራጫል። መራርነት ወደ ልብ ከሚገቡ ክፉ ነገሮች መካከል ጥሩ ምሳሌ ነው። በመራርነትና ይቅር ባለማለት የተሞላን ሰው መለየት ቀላል ነው። ልቡ ያንን መራርነት ወደ አገልግሎቱ ያሰራጫል እናም የመለየት አቅም ላለው ዓይን በግልጽ የሚታይ ነው። በሚናገርበት ጊዜ ምሬቱን ታሸታለህ። በሚሰብክበት ጊዜ በስብከቱ ውስጥ ይገለጣል። ወደ ልብህ ስለሚገባው ነገር ተጠንቀቅ።

8. **የሰው የተፈጥሮ ልብ በከፍተኛ ስብ ምክንያት ይታመማል።** ይህ የሚያሳየን መጋቢ ስለ ብልጽግና እጅግ ብዙ መልዕክቶችን መስማት ሲጀምር ልቡ ይታመማል። የክርስቶስ አካል ከብዙ የብልጽግና ትምህርቶች የተነሳ የልብ ህመም ገጥሟታል።

9. **አነስተኛ የሰውነት እንቅስቃሴ በሚያደርጉ ሰዎች የሰው የተፈጥሮ ልብ ለበሽታ የተጋለጠ ነው።** ይህ እውነት መንፈሳዊ ልብ ብዙ የእግዚአብሔርን ቃል ሲቀበልና ነገር ግን ወደ ተግባር

በማይተረጉምበት ጊዜ እንደሚታመም ያሳየናል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የልብ ህመም የሚያውቀውን በማይኖር ሰው ህይወት የመከሰት እድሉ የሰፋ ነው፡፡ የሚሲዮናዊነት አገልግሎት መንደል፣ የወንጌል ሥርጭት አገልግሎት መንደል፣ እና የወንጌል ማዳረስ አገልግሎት መንደል በክርስቶስ አካል ላይ የልብ ህመም አስከትሏል፡፡

10. አልኮል መጠጥ በሚወስዱ ሰዎች ህይወት የሰው የተፈጥሮ ልብ ለሕመም የተጋለተ ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ መንፈሳዊ ልብ በህይወታችን ማታለልንና ግራ መጋባትን በሚያባዛው የዚህ አለም ደስታ መርዝ ሊጠቃ ይችላል፡፡

## ምዕራፍ 38

# የእረኞች ልብ አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድነው?

"አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ፥ የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነውና።"

ምሳሌ 4፡23

1. ልብን ስለመጠበቅ ብርቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስጠንቀቂያ ስላለ የመጋቢዎች ልብ ትኩረት የሚሻ ነገር ነው፡፡ ማንኛውም በከፍተኛ ደረጃ ጥበቃ የሚደረግለት ነገር አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ በአንድ ህንጻ ዙሪያ ያለው የጥበቃ ሁኔታ የህንጻውን አስፈላጊነት ደረጃ ያመለክታል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ልብን ስለመጠበቅ የሚሰጠው ጠንካራ ማስጠንቀቂያ ልብ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ያሳየናል፡፡

አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ፥ የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነውና።

ምሳሌ 4፡23

2. ልብ የአገልግሎት ምንጭ በመሆኑ የመጋቢ ልብ ትኩረት የሚሻ ነገር ነው፡፡

"አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ፥ የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነውና።"

ምሳሌ 4፡23

3. ልብ የነገሮችና ችግሮች መነሻ በመሆኑ የመጋቢ ልብ ትኩረት የሚሻ ነገር ነው፡፡ አሁን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካሉ ችግሮቻችን አብዛኛዎቹ ከልብ የሚወጡ ናቸው፡፡ስለሆነም ችግሮች መወገድ ያለባቸው በልብ ውስጥ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ግን ከሥር መሰረቱ በልብ ውስጥ ያለውን ቅሬታ ሳይፈታ ችግሮችን ላይ ላዩን ለመፍታት ይሞከራል፡፡ ለዚህ ነው ችግሩ ያለማቋረጥ የሚቀጥለው፡፡

"አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ፥ የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነውና።"

ምሳሌ 4፡23

4. **ልብ መላ ህይወትን የሚቆጣጠር በመሆኑ የመጋቢ ልብ ትኩረት የሚሻ ነገር ነው።**

"አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ፥ የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነውና።"

ምሳሌ 4፡23

5. **ልብ የህይወት መጀመሪያ በመሆኑ የመጋቢ ትኩረት የሚሻ ነገር ነው። አገልግሎትህ ህይወት የተሞላበት ከሆነ ልብህ ህይወት የተሞላ ነው ማለት ነው።**

"አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ፥ የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነውና።"

ምሳሌ 4፡23

6. **ልብ ማንም ሊያውቀው የማይችል በመሆኑ የመጋቢ ልብ ትኩረት የሚሻ ነገር ነው።**

"የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ እጅግም ክፉ ነው ማንስ ያውቀዋል?"

ኤርሚያስ 17፡9

"አቤቱ፥ መርምረኝ ልቤንም እወቅ ፍተነኝ መንገዴንም እወቅ"

መዝሙር 139፡23

7. **ብዙ የተሰወረ መዝገብ በውስጡ የያዘ ሣጥን በመሆኑ የመጋቢ ትኩረት የሚሻ ነገር ነው። የተሰወረ መዝገብ ዋጋቸው የከበረና አንዳንዴም የጥንታዊ ቁሳቁሶች ስብስብ ነው። ልብ ለብዙ ጊዜያት የቆዩ ዋጋ ያላቸውና ጠቃሚ ነገሮችን ይዟል። ምንም እንኳ ብዙ ጠቃሚ ነገሮችን የያዘ ቢሆንም ልብ ከእይታችን የተሰወረ ነው። የመጋቢውም ልብ እንደዚሁ ነው። ሊሰሩት ወይም ሊያፈርሱት የሚችሉ ጠቃሚ ንጥረ ነገሮች በልቡ ውስጥ አሉ።**

መልካም ሰው ከልቡ መልካም መዝገብ መልካም ነገርን ያወጣል፥ ክፉ ሰውም ከክፉ መዝገብ ክፉ ነገርን

ማቴዎስ 12፡35

8. **ልብ የብዙ ክፉ ነገሮች ምንጭም ሊሆን ስለሚችል የመጋቢ ልብ ትኩረት የሚሻ ነገር ነው። ልብ የመልካምም የክፉም ነገሮች መውጫ ነው። ሰዎች የሚሰሯቸው ክፋቶች መነሻ**

ልባቸው ነው። ልብ ደህንነትን ሲያገኝና ሲለወጥ የክፋት ምንጭ ይደርቃል።

ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣ ክፉ አሳብ፥ ዝሙት፥ መስረቅ፥ መግደል፥ ምንዝርነት፥ መጐምጀት፥ ክፋት፥ ተንኰል፥ መዳራት፥ ምቀኝነት፥ ስድብ፥ ትዕቢት፥ ስንፍና ናቸውና፤ ይህ ክፉው ሁሉ ከውስጥ ይወጣል ሰውን ያረክሰዋል።

ማርቆስ 7፡21-23

9. የእግዚአብሔር መኖሪያ ሊሆን ስለሚችል የመጋቢ ልብ ትኩረት የሚሻ ነገር ነው። እግዚአብሔር በልባችን ለመኖር ወዷል። ይህም ልባችንን ትኩረት የሚሻ ያደርገዋል። እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ከሆነ በልብህ ውስጥ ነው ያለው። እግዚአብሔር ሲናገርህ የሚናገረው ለልብህ ነው። ይህም ልብህ ተፈላጊ ሥፍራ መሆኑን ያሳያል። በልብህ ውስጥ ሌላ ማንም እንደሌለ እርግጠኛ ሁን። በልብህ ውስጥ ከክርስቶስ ሌላ ምንም ነገር እንደሌለ እርግጠኛ ሁን።

“ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር እንደ ክብሩ ባለ ጠግነት መጠን ይሰጣችሁ፤ የእናንተ ሥርና መሠረት በፍቅር ይጸና ዘንድ፥”

ኤፌሶን 3፡17

“እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ፥ ወደ እርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል።”

ራእይ 3፡20

10. የአጋንንት ማደሪያም ሊሆን ስለሚችል የመጋቢ ልብ ትኩረት የሚሻ ነገር ነው። ልብ የእረኩሳን መናፍስት ማደሪያም ሊሆን ይችላል። አሁንም በድጋሚ ይህ ልብ ትኩረት እንደሚያስፈልገው የሚያመላክት እውነት ነው።

“ርኩስ መንፈስ ግን ከሰው በወጣ ጊዜ፥ ዕረፍት እየፈለገ ውኃ በሌለበት ቦታ ያልፋል፥ አያገኝምም። በዚያን ጊዜም። ወደ ወጣሁበት ቤቴ እመለሳለሁ ይላል፤ ቢመጣም ባዶ ሆኖ ተጠርጎና አጊጦ ያገኘዋል። ከዚያ ወዲያ ይሄድና ከእርሱ የከፉትን ሰባት ሌሎችን አጋንንት ከእርሱ ጋር ይወስዳል፥ ገብተውም በዚያ ይኖራሉ፤ ለዚያም ሰው ከፊተኛው ይልቅ የኋለኛው ይብስበታል። ለዚህ ክፉ ትውልድ ደግሞ እንዲሁ ይሆንበታል።”

ማቴዎስ 12፡ 43-45

## *ምዕራፍ 39*

# ንጹህ ልብ ይኑርህ

መጽሐፍ ቅዱስ ስለተለያየ አይነት ልብ ይናገራል። ትክክለኛው አይነት ልብ ይኖረህ ዘንድ በልብህ ላይ ትኩረት አድርገህ መስራት ያስፈልግሀል። ያለ ትክክለኛ ልብ ለጌታ ብዙ ልትሰራለት አትችልም። ልብ የአገልግሎትህ ማዕከል በመሆኑ የድካምህን ውጤት ሁሉ የሚወስነው እርሱ ነው።

1. **ፈቃደኛ ልብ ይኑርህ። ፈቃደኛ ልብ ራሱን ለአንድ ነገር የሚሰጥ ልብ ነው።**

"ስጦታ ያመጡልኝ ዘንድ ለእስራኤል ልጆች ተናገር በገዛ እጁ ሊሰጠኝ በልቡ ከሚያምረው ሰው ሁሉ መባ ተቀበሉ።"

ዘጸአት 25፡2

2. **የተነሳሳ ልብ ይኑርህ። የተነሳሳ ልብ የውስጥ ስሜቱን በደስታ የሚገልጽና የሚንቀሳቀስ ልብ ነው።**

ከእነርሱም ሰው ሁሉ ልቡ እንዳነሣሣው መንፈሱም እሺ እንዳሰኘው ለመገናኛው ድንኳን ሥራ ለማገልገያውም ሁሉ ለተቀደሰውም ልብስ ለእግዚአብሔር ስጦታ አመጡ።

ዘጸአት 35፡21

3. **ሩህሩህ ልብ ይኑርህ። ሩህሩህ ልብ ቸርና የሚራራ ልብ ነው። ሩህሩህ ልብ አስታራቂ ልብ ነው።**

"እግዚአብሔር ልቤን አባብቶታልና፥ ሁሉንም የሚችል አምላክ አስደንግጦኛል።"

ኢዮብ 23፡16

4. **ተግባቢ ልብ ይኑርህ። ተግባቢ ልብ የቅርብ ግንኙነት ማድረግ የሚያስችል ልብ ነው። ተግባቢ ልብ ከእግዚአብሔር ጋር የመቀራረብ ሁኔታ ውስጥ ያለ ልብ ነው።**

"ተቈጡ፥ ነገር ግን ኃጢአትን አታድርጉ በመኝታችሁ ሳላችሁ በልባችሁ አስቡ ዝም በሉ።"

መዝሙር 4፡4

## 5. እንደ ሰም ያለ ልብ ይኑርህ። እንደ ሰም የሆነ ልብ ግትር ያልሆነ ልብ ነው። አንዳንድ ባህሪያት፣ ጠባያትና ሁኔታዎች ሊያጋጥሙት እንደሚችሉ ግምት ውስጥ የሚያስገባ ነው።

"እንደ ውኃ ፈሰስሁ አጥንቶቼም ሁሉ ተለያዩ ልቤ እንደ ሰም ሆነ፥ በአንጀቴም መካከል ቀለጠ።"

መዝሙር 22፡14

## 6. የሚቃጠል ልብ ይኑርህ። የሚቃጠል ልብ የተነቃቃ ስሜት ወይም ፍላጎት ያለው ልብ ነው።

"እርሱም፦ እናንተ የማታስተውሉ፥ ነቢያትም የተናገሩትን ሁሉ ልባችሁ ከማመን የዘገየ፤ ክርስቶስ ይህን መከራ ይቀበል ዘንድና ወደ ክብሩ ይገባ ዘንድ ይገባው የለምን? አላቸው። ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ ስለ እርሱ በመጻሕፍት ሁሉ የተጻፈውን ተረጐመላቸው። ወደ ሚሄዱበትም መንደር ቀረቡ፥ እርሱም ሩቅ የሚሄድ መሰላቸው። እነርሱ፦ ከእኛ ጋር እደር፥ ማታ ቀርቦአልና ቀኑም ሊመሽ ጀምሮአል ብለው ግድ አሉት፤ ከእነርሱም ጋር ሊያድር ገባ። ከእነርሱም ጋር በማዕድ ተቀምጦ ሳለ እንጀራውን አንሥቶ ባረከው፥ ቈርሶም ሰጣቸው፤ ዓይናቸውም ተከፈተ፥ አወቁትም፤ እርሱም ከእነርሱ ተሰወረ። እርስ በርሳቸውም። በመንገድ ሲናገረን መጻሕፍትንም ሲከፍትልን ልባችን ይቃጠልብን አልነበረምን? ተባባሉ።"

ሉቃስ 24፡25-32

## 7. በእግዚአብሔር ከተጠሩ ጋር አንድ ልብ ይኑርህ። ይህ ከወንድሞች ጋር የሚተባበርና አንድነት ያለው ልብ ነው።

"ያመኑትም ሕዝብ አንድ ልብ አንዲትም ነፍስ ነበሩአቸው፥ ገንዘባቸውም ሁሉ በአንድነት ነበረ እንጂ ካለው አንድ ነገር ስንኳ የራሱ እንደ ሆነ ማንም አልተናገረም።"

የሐዋርያት ሥራ 4፡32

## 8. የተከፈተ ልብ ይኑር። የተከፈተ ልብ እግዚአብሔር ወደ ውስጡ እንዲገባ የሚፈቅድ ልብ ነው። የተዘጋ፣ የተጠረዘ፣ ወይም የታሸገ ልብ አይደለም። የዚህ ዓይነቱ ልብ ነገሮችን ለማገናዘብ ፈቃደኛና የተዘጋጀ ልብ ነው። እግዚአብሔር እንዲጠቀምበት ራሱን ያቀረበና የተዘጋጀ ልብ ነው።

"ከትያጥሮን ከተማም የመጣች ቀይ ሐር ሻጭ እግዚአብሔርን የምታመልክ ልድያ የሚሉአት አንዲት ሴት ትሰማ ነበረች፤ ጳውሎስም የሚናገረውን ታዳምጥ ዘንድ ጌታ ልብዋን ከፈተላት።"

የሐዋርያት ሥራ 16:14

9. **የሚታዘዝ ልብ ይኑርህ፡፡ ታዛዥ ልብ ከእግዚአብሔር ትዕዛዝና መመሪያ ጋር በተግባር የሚስማማ ልብ ነው፡፡ ለእግዚአብሔር አብ ሥልጣንና ፈቃድ ራሱን የሚያስገዛ ልብ ነው፡፡**

"ነገር ግን አስቀድማችሁ የኃጢአት ባሪያዎች ከሆናችሁ፥ ለተሰጣችሁለት ለትምህርት ዓይነት ከልባችሁ ስለ ታዘዛችሁ፥ ከኃጢአትም አርነት ወጥታችሁ ለጽድቅ ስለ ተገዛችሁ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን።"

ሮሜ 6:17

10. **የጸና ልብ ይኑርህ፡፡ የጸና ልብ ያለመናወጥ የሚረጋጋ፣ ጽኑና የማይነቃነቅ ልብ ነው፡፡ ታማኝና የማያወላውል ልብ ነው፡፡**

"ሳይናወጥ በልቡ የጸና ግን ግድ የለበትም፥ የወደደውን እንዲያደርግ ተፈቅዶለታል፤ ድንግልናውንም በልቡ ይጠብቅ ዘንድ ቢጸና፥ መልካም አደረገ።"

1ኛ ቆሮንቶስ 7:37

## ምዕራፍ 40

# አልበገር ባይ ልብን አስወግድ

መጽሐፍ ቅዱስ ስለተለያየ አይነት እልኸኛ ልቦችም ይናገራል። አልበገር ባይ ልብን ለማስወገድ በልብህ ላይ ትኩረት አድርገህ ልትሰራ ይገባል። ያለትክክለኛ ልብ ለጌታ ብዙ ልታደርግለት አትችልም። ልብህ ያገልግሎትህ ማዕከል በመሆኑ የምታደርገው ነገር ሁሉ ውጤቱ የሚመሰረተው በልብህ ላይ ነው። በእርግጥም አልበገር ባይ ልብን ማስወገድ አለብህ። ከዚህ ቀጥሎ እንደምናየው አልበገር ባይ ልቦች ከልቦች ሁሉ እጅግ አስቀያሚ ልቦች ናቸው።

1. **ደንዳና ልብን አስወግድ። ደንዳና ልብ በቀላሉ የማይታለፍ ስሜተቢስ ልብ ነው። ደንዳና ልብ ጫና ቢደረግበትም የማይበገር ልብ ነው።**

"እግዚአብሔርም ሙሴን አለው፦ወደ ግብፅ በምትመለስበት ጊዜ በሰጡህ ኃይል የምትሰራቸውን ታምራት ሁሉ በፈርዖን ፊት መፈጸም እንዳለብህ አትዘንጋ። እኔ ግን ሕዝቡን እንዳይለቅ ልቡን አደነድነዋለሁ።"

ዘጸአት 4፡21 (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

2. **አመፀኛ ልብን አስወግድ። አመፀኛ ልብ ቁጥጥርንና ሥልጣንን ጥላሸት የሚቀባ፣በእምቢታ የሚቃወም ልብ ነው።**

"ለዚህ ሕዝብ ግን የሸፈተና ያመፀ ልብ አላቸው ዐምፀዋል ሄደውማል።"

ኤርምያስ 5፡23

3. **ድንጋይ ልብን አስወግድ። ድንጋይ ልብ ቀዝቃዛና ምላሽ የማይሰጥ እንዲሁም ከራሱ ውጭ ለሚመጣ ለማንኛውም ተጽዕኖ ስሜት የማይሰጥ ተቃውሞ ያለው ልብ ነው። ድንጋይ ልብ የተለሳለሰ ስሜት የሌለው ልብ ነው።**

አንድ ልብ እሰጣቸዋለሁ፥ በውስጣቸውም አዲስ መንፈስ እሰጣለሁ፥ ከሥጋቸውም ውስጥ የድንጋዩን ልብ አወጣለሁ የሥጋንም ልብ እሰጣቸዋለሁ

ሕዝቅኤል 11፡19

## 4. ኩራተኛ ልብን አስወግድ። ኩራተኛ ልብ ትዕቢተኛና እብሪተኛ ልብ ነው።

"ባልንጀራውን በቀስታ የሚያማን እርሱን አሳደድሁ በዓይኑ ትዕቢተኛ የሆነውና ልቡ የሚሳሳው ከእኔ ጋር አይተባበርም።"

መዝሙር 101፡ 5

## 5. የጨለመ ልብን አስወግድ። የጨለመ ልብ ንቃት፣ እውቀት ወይም ሥልጣኔ የጎደለው ነው። አደገኛና ከፉ ልብ ነው።

"ስለዚህም እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት የማያመካኙት አጡ፤ ነገር ግን በአሳባቸው ከንቱ ሆኑ የማያስተውለውም ልባቸው ጨለመ።"

ሮሜ 1፡21

## 6. የማያምንን ልብ አስወግድ። የማያምን ልብ በጥያቄ የተሞላና ተጠራጣሪ ልብ ነው።

ወንድሞች ሆይ፥ ምናልባት ሕያው እግዚአብሔርን የሚያስከዳችሁ ክፉና የማያምን ልብ ከእናንተ በአንዳችሁ እንዳይኖር ተጠንቀቁ!

ዕብራውያን 3፡12

# ምዕራፍ 41

# ጤናማ ልብ ይኑርህ

መጽሐፍ ቅዱስ ስለተለያዩ አይነት ልቦች ይናገራል። ጤናማ ልብ ይኖርህ ዘንድ በልብህ ላይ ትኩረት አድረገህ መስራት ይጠበቅብሃል። ያለትክክለኛ ልብ ለጌታ ብዙ ልታደርግለት አትችልም። ልብህ ያገልግሎትህ ማዕከል በመሆኑ የምታደርገው ነገር ሁሉ ውጤቱ የሚመሰረተው በልብህ ላይ ነው።

1. **የይቅርታ ልብ ይኑርህ። የይቅርታ ልብ ምህረት ለማድረግ የሚችል ልብ ነው።**

"ከእናንተ እያንዳንዱ ወንድሙን ከልቡ ይቅር ካላለ፥ እንዲሁ ደግሞ የሰማዩ አባቴ ያደርግባችኋል።"

ማቴዎስ 18፡35

2. **ንጹህ ልብ ይኑርህ። ንጹህ ልብ ከማንኛውም ከሚያቆሽሽ ነገር የፀዳ ነው። ከማንኛውም ብክለት ነጻ የሆነ ዕዱና ንጹህ ልብ ነው።**

"እጆቹ የነጹ፥ ልቡም ንጹሕ የሆነ፥ ነፍሱን ለከንቱ ያላነሣ፥ ለባልንጀራውም በሽንገላ ያልማለ።"

መዝሙር 24፡4

3. **ፍጹም ልብ ይኑርህ። ፍጹም ልብ ፈጽሞ ስህተት ፣ ግድፈት ወይም ነቀፋ የሌለበት ልብ ነው።**

"እነዚህ ሁሉ ዳዊትን በእስራኤል ሁሉ ላይ ያነግሡት ዘንድ አርበኞችና ሰልፈኞች እየሆኑ በፍጹም ልባቸው ወደ ኬብሮን መጡ ደግሞም ከእስራኤል የቀሩት ሁሉ ዳዊትን ያነግሡት ዘንድ አንድ ልብ ነበሩ።"

1ኛ ዜና መዋዕል 12፡38

4. **ቅን ልብ ይኑርህ። ቅን ልብ በጠንካራ ሥነምግባር በተሞላ ባሕሪ ይታወቃል። እውነተኛና የተከበረ ልብ ነው።**

"ቃሌ የልቤን ቅንነት ያወጣል ከንፈሮቼም የሚያውቁትን በቅንነት ይናገራሉ።"

ኢዮብ 33፥3

5. **ህያው ልብ ይኑርህ። ህያው ልብ ህይወት ያለበትና በሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያለ ልብ ነው።**

"ችግረኞች ያያሉ ደስ ይላቸዋል እግዚአብሔርን ፈልጉ ሕያዋንም ሁኑ።"

መዝሙር 69፥32

6. **ትሁት ልብ ይኑርህ። ትሁት ልብ በመልካም ሁኔታ ላይ የሚገኝ ከስንጥቅ ከጉድለት ወይም ከጉዳት የጸዳ ነው።**

"ትሑት ልብ የሥጋ ሕይወት ነው ቅንዓት ግን አጥንትን ያነቅዛል።"

ምሳሌ 14፥30

7. **አዲስ ልብ ይኑርህ። አዲስ ልብ ሲባል በእግዚአብሔር ኃይል የተፈጠረ ልብ ማለት ነው። አሮጌውን ልብ ከነሥራው ለመተካት የተሰጠ አዲስ ልብ ነው።**

"የእስራኤል ቤት ሆይ፥ ስለዚህ እንደ መንገዱ በየሰዉ ሁሉ እፈርድባችኋለሁ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር ንስሐ ግቡ ኃጢአትም ዕንቅፋት እንዳይሆንባችሁ ከኃጢአታችሁ ሁሉ ተመለሱ። የበደላችሁትን በደል ሁሉ ከእናንተ ጣሉ አዲስ ልብና አዲስ መንፈስም ለእናንተ አድርጉ የእስራኤል ቤት ሆይ፥ ስለ ምን ትሞታላችሁ? የምዋቹን ሞት አልፈቅድምና፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር ስለዚህ ተመለሱና በሕይወት ኑሩ።"

ሕዝቅኤል 18፥30-32

8. **የማይነቀፍ ልብ ይኑርህ። የዚህ አይነቱ ልብ በማንኛውም መልኩ ስህተተኛ ፣ ክፉ ወይም የሚያቆስል ያልሆነ ልብ ነው።**

"ጌታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅዱሳኑ ሁሉ ጋር ሲመጣ፥ በአምላካችንና በአባታችን ፊት በቅድስና ነቀፋ የሌለበት አድርጎ ልባችሁን ያጸና ዘንድ"

1ኛ ተሰሎንቄ 3፥13

9. **በደሙ የተረጨ ልብ ይኑርህ። የዚህ አይነቱ ልብ በእግዚአብሔር ኃይል የነጻ ልብ ነው።**

"ከክፉ ሕሊና ለመንጻት ልባችንን ተረጭተን ሰውነታችንንም በጥሩ ውኃ ታጥበን በተረዳንበት እምነት በቅን ልብ እንቅረብ፤"

ዕብራውያን 10፥22

## 10. የተቀደሰ ንጹህ ልብ ይኑርህ። የተቀደሰ ንጹህ ልብ ቅዱስና ከኃጢአትና ከወቀሳ የጸዳ ልብ ነው።

"ለእውነት እየታዘዛችሁ ግብዝነት ለሌለበት ለወንድማማች መዋደድ ነፍሳችሁን አንጽታችሁ እርስ በርሳችሁ ከልባችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ።"

1ኛ ጴጥሮስ 1፡22

## ምዕራፍ 42

# ከህመምተኛ ልብ ተፈወስ

በመሠረቱ በርካታ አይነት የልብ ችግሮች አሉ። ከልብ ህመም ነጻ ትሆን ዘንድ ልብህ ላይ ትኩረት አድርገህ ጠንክረህ መስራት አለብህ። ያለ ጤናማና የሚሰራ ልብ ለጌታ ብዙ ልትሰራለት አትችልም። የልብ ህመምተኞች ብዙ ማከናወን የማይችሏቸው ነገሮች አሉ። በልብህ ውስጥ ያለ በሽታ ሁሉ በአገልግሎትህ ላይ መገለጡ አይቀርም።

1. **ከሳተ ልብ የተፈወስክ ሁን። የሳተ ልብ ውሸት የሆነን ነገር እውነተኛና ዋጋ ያለው አድርጎ የተቀበለ የተወናበደ ልብ ነው።**

"ልባችሁ እንዳይስት፥ ፈቀቅ እንዳትሉ፥ ሌሎችንም አማልክት እንዳታመልኩ፥ እንዳትሰግዱላቸውም፥"

ዘዳግም 11፥16

2. **ከማያስተውል ልብ የተፈወስክ ሁን። የማያስተውል ልብ ብዙ ነገሮችን መረዳት የማይችል ልብ ነው። የእግዚአብሔርን ነገር የማይረዳ፣ የማይመረምር ወይም የማያስተውል ልብ ነው።**

"እግዚአብሔር ግን አስተዋይ ልብ፥ የሚያዩ ዓይኖች፥ የሚሰሙም ጆሮች እስከ ዛሬ ድረስ አልሰጣችሁም።"

ዘዳግም 29፡4

3. **ከሰባና ከደነደነ ልብ የተፈወስክ ሁን። የዚህ አይነቱ ልብ ደንዛዝና የማይገባው ነው።**

"ልባቸው የሰባና የደነደነ ነው፤ እኔ ግን በሕግህ ደስ ይለኛል።"

መዝሙር 119፡ 70

4. ከመራራ ልብ የተፈወስክ ሁን። መራራ ልብ ሻካራና የሚተች ልብ ነው። መራራ ልብ በተወሰኑ ሰዎች ላይ ባለ ከፍተኛ ጥላቻም ይገለጣል።

"እያንዳንዱ ልብ የራሱን መራራ ሀዘን ያውቃል፤ ደስታውንም ማንም ሊጋራው አይችልም።"

ምሳሌ 14፡10

"ስለ አንቺም የራሳቸውን ጠጉር ይላጫሉ፤ ማቅም ያሸርጣሉ፤ በነፍስ ምሬትም ስለ አንቺ መራራ ልቅሶ ያለቅሳሉ።"

ሕዝቅኤል 27፡31 (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

5. ከቆሰለ ልብ የተፈወስክ ሁን። የቆሰለ ልብ የተጠቃና የሚሰቃይ ነው። አንዳንድ አጋጣሚዎች የጎዱት ልብ ነው።

"እኔ ድኻና ችግረኛ ነኝና፤ ልቤም በውስጤ ቆስሎአልና።"

መዝሙር 109 ፡ 22 (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

6. ከደካማ ልብ የተፈወስክ ሁን። ደካማ ልብ ጥንካሬ እና ሐይል የጎደለው ልብ ነው። ጫናና ጭንቀት ከገጠመው ሊሰበር የሚችል ልብ ነው።

"የማታፍረውን የጋለሞታን ሥራ ሁሉ ሠርተሻልና ልብሽ ምንኛ ደካማ ነው? ይላል ጌታ እግዚአብሔር፦ በየመንገዱ ራስ የምንዝርናሽን ስፍራ ሠርተሻል፤ በየአደባባዩም ከፍ ያለውን ቦታሽን አድርገሻል። ዋጋዋን እንደምትንቅ እንደ ጋለሞታ አልሆንሽም።"

ሕዝቅኤል 16፡30-31

7. ከድፍድፍ ልብ የተፈወስክ ሁን። የዚህ አይነቱ ልብ ያልጠራና ንቃት ወይም ክፉና ደጉን የመለየት አቅም የሌለው ልብ ነው።

በዓይናቸው እንዳያዩ፥ በጆሮአቸውም እንዳይሰሙ፥ በልባቸውም እንዳያስተውሉ፥ ተመልሰውም እንዳልፈውሳቸው፥ የዚህ ሕዝብ ልብ ደንድኖአልና ጆሮአቸውም ደንቁሮአል፤ ዓይናቸውንም ጨፍነዋል የሚል የኢሳይያስ ትንቢት በእነርሱ ይፈጸማል።

ማቴዎስ 13፡15

8. በክፉ ምኞት ከሚጠመድ ልብ የተፈወስክ ሁን። ክፉ የሚመኝ ልብ ክፉ በማድረግና በስስት የተሞላ ነው። ልቡ ሳያቋርጥ ስለ ወሲብ የሚያስብ ነው።

"እንደ ልባቸው ሥራ ተውኋቸው፥ በልባቸውም አሳብ ሄዱ።"

መዝሙር 81፡12

9. ከአመንዝራ ልብ የተፈወስክ ሁን። ይህ ደግሞ የማይታመን ልብ ነው።

"ከልብ ክፉ አሳብ፥ መግደል፥ ምንዝርነት፥ ዝሙት፥ መስረቅ፥ በውሸት መመስከር፥ ስድብ ይወጣልና።"

ማቴዎስ 15፡19

10. እግዚአብሔርን ማየት ከተሳነው ልብ የተፈወስክ ሁን። ይህ አይነቱ ልብ የእግዚአብሔርን ነገር ለማየት፣ ለመቀበልና ለመረዳት የማይፈቅድና የማይችል ነው።

"እነርሱ ባለማወቃቸው ጠንቅ በልባቸውም ደንዳንነት ጠንቅ ልቡናቸው ጨለመ፥ ከእግዚአብሔርም ሕይወት ራቁ፤"

ኤፌሶን 4፡18

11. በነገሮች ከተዋጠ ልብ የተፈወስክ ሁን። የዚህ አይነቱ ልብ በስሜትና በሁኔታዎች ፈጽሞ የሚዋጥ ልብ ነው።

"ልቤ ተሰፋ በቈረጠ ጊዜ ከምድር ዳርቻ ወደ አንተ እጮኻለሁ፤ በድንጋይ ላይ ከፍ ከፍ አደረግኸኝ።"

መዝሙር 61፡2

12. ከጣዖት አምላኪ ልብ የተፈወስክ ሁን። ጣዖትን የሚያመልክ ልብ የማይረካ ከዓለም ደስታን ፍለጋ የሚቅበዘበዝ ልብ ነው።

"እዚያም በስደት ይኖራሉ፤ እዚያ በሚኖሩበትም ጊዜ እኔን ያስታውሳሉ፤ እኔም የቀጣኋቸውና እነርሱን ያዋረድኋቸው ልባቸው ከዳተኛ በመሆኑና እኔን ትተው ጣዖታትን በመምረጣቸው ምክንያት መሆኑን ይገነዘባሉ፤ ካደረጉትም ክፉትና ከፈጸሙት አሳፋሪ ነገር የተነሣ ራሳቸውን ይጸየፋሉ።"

ሕዝቅኤል 6፡9 (አዲሱ ትርጉም 1980)

## ምዕራፍ 43

# የሚያበረታ ልብ ይኑርህ

የሚያበረታ ልብ እንዲኖርህ ማድረግ ትችላለህ። በሚያበረታ ልብ ለጌታ ብዙ ነገር ልታደርግ ትችላለህ። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ዘጠኝ አይነት የሚያበረቱ ልቦች ይነግረናል።

**1. የሥጋ ልብ ይኑርህ። የሥጋ ልብ ለስላሳው የሰው ውስጠኛ ክፍል ነው። ውጫዊው ክፍል ጠንካራ ቢመስልም እንኳ የሰው ውስጣዊ ክፍል ለስላሳ መሆኑ ጠቃሚ ነው።**

"በትእዛዜም ይሄዱ ዘንድ ፍርዴንም ይጠብቁና ያደርጉ ዘንድ አንድ ልብ እሰጣቸዋለሁ፥ በውስጣቸውም አዲስ መንፈስ እሰጣለሁ፥ ከሥጋቸውም ውስጥ የድንጋዩን ልብ አወጣለሁ፤ የሥጋንም ልብ እሰጣቸዋለሁ። እነርሱም ሕዝብ ይሆኑኛል፤ እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ።"

ሕዝቅኤል ፲፩:19-20

**2. ስለሌሎች የሚገደው ልብ ይኑርህ። ስለሌሎች የሚገደው ልብ ሌሎች የሚቆረቆርና የሌላውን ችግር እንደራሱ አድርጎ የሚመለከት ልብ ነው።**

"እኔ ለእናንተ ያለኝን በጎ ሀሳብ በቲቶ ልብ ውስጥ ያኖረ አምላክ የተመሰገነ ይሁን።"

2ኛ ቆሮንቶስ 8:16

**3. የሚዘምር ልብ ይኑርህ። የሚዘምር ልብ ያለማቋረጥ ለጌታ የሚቀኝ ልብ ነው። የሚዘምር ልብ ደስተኛ ነው።**

"በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ እርስበርሳችሁ ተነጋገሩ፤ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ፤"

ኤፌሶን 5:19

**4. ለስላሳ ልብ ይኑርህ። ለስላሳ ልብ በተለይ ለደካሞች፣ ድሆችና ለተቸገሩ ፍቅርና ርህራሄ የሚያሳይ ነው።**

"በፊቴም ራስህን አዋርደሃልና፥ በዚህም ስፍራና በሚኖሩበት ላይ ቃሌን በሰማህ ጊዜ ራስህን አዋርደሃልና፥ ልብስህንም ቀድደህ በፊቴ አልቅሰሃልና እኔ ደግሞ ሰምቼአለሁ፥ ይላል እግዚአብሔር፡-"

1ኛ ቆሮንቶስ 34፡27

5. **የሚያውጅ ልብ ይኑርህ። አዋጅ ተናጋሪ ልብ ለህዝብ ወንጌልን የሚያደርስ ልብ ነው። አዋጅ ተናጋሪ ልብ ያለው ሰው ድምጹ በጉልህ የሚሰማና ስለሌሎች መዳን የሚገደድ ነው።**

"ልቤ መልካም ነገርን አፈለቀ፥ እኔ ሥራዬን ለንጉሥ እነግራለሁ፤ አንደበቴ እንደ ፈጣን ጸሓፊ ብርዕ ነው።"

መዝሙር 45፡1

6. **ደስተኛ ልብ ይኑርህ። ደስተኛ ልብ ፈጣንና ኃይል የተሞላ ነው። በመንፈስ ሀሴት ያደርጋል።**

"ደስ ያላት ልብ መልካም መድኃኒት ናት። ያዘነች ነፍስ ግን አጥንትን ታደርቃለች።"

ምሳሌ 17፡22

7. **መልካምና እውነተኛ ልብ ይኑርህ። እውነተኛ ልብ ያለው ሰው ሁጊዜ እውነትን ይናገራል እንጂ ሰዎችን ለማታለል ወይም ህግ ለመጣስ አይሞክርም። እውነተኛ ልብ ፍጹም እውነትን የሚናገርና ሌሎችን ባያስደስትም ቀጥተኛ አስተያየቱን የሚገልጥ ነው።**

"በመልካም መሬት ላይም የወደቀ እነርሱ በመልካምና በበጎ ልብ ቃሉን ሰምተው የሚጠብቁት በመጽናትም ፍሬ የሚያፈሩ ናቸው።"

ሉቃስ 8፡15

8. **የተገረዘ ልብ ይኑርህ። የተገረዘ ልብ ያለው ሰው ከህይወቱ የተበላሹና አላስፈላጊ የሆኑ ነገሮች የተወገዱለት ሰው ነው፡ ፡**

"ዳሩ ግን በስውር አይሁዳዊ የሆነ አይሁዳዊ ነው፥ መገረዝም በመንፈስ የሚደረግ የልብ መገረዝ ነው እንጂ በመጽሐፍ አይደለም፤ የእርሱ ምስጋና ከእግዚአብሔር ነው እንጂ ከሰው አይደለም።"

ሮሜ 2፡29

9. ሰፊ ልብ ይኑርህ። ሰፊ ልብ ከተለመደው ልብ የላቀ መጠን ያለው ነው። ሰፊ ልብ ያለው ሰው ከሁሉም አይነት ሰው ጋር ለመግባባት አቅም ያለው ሲሆን መበደልን፣ አለመመቸትን፣ መዋረድን ወይም ጉስቁልናን የሚሸከም ትከሻ አለው።

"እናንተ የቆሮንቶስ ሰዎች ሆይ፥ አፋችን ለእናንተ ተከፍቶአል፤ ልባችንም ሰፍቶላችኋል፤"

2ኛ ቆሮንቶስ 6፡11

## ምዕራፍ 44

# ከአሉታዊ ልብ ተጠንቀቅ

አሉታዊ ስለሆኑ የተለያዩ የልብ አይነቶች መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይነግረናል። የዚህ አይነቱ አሉታዊ ልብ እንዳይኖርህ በልብህ ላይ ትኩረት አድርገህ መስራት አለብህ። ያለትክክለኛ ልብ ለጌታ ብዙ ልታደርግለት አትችልም። አሉታዊ ልብ የአገልግሎትህን ማዕከል ከያዘ የሰይጣንን ኃይል ወደ አገልግሎትህ ይረጫል። እስኪ አሁን የሚከተሉትን አሥራ አራት አይነት የአሉታዊ ልብ አይነቶች እንመልከት።

1. **ከአይን አውጣ ልብ ተጠንቀቅ። አይን አውጣልብ አጉል የሚደፍርና ከተፈቀደለት ከሚገባው ገደብ አልፎ የሚሄድ ልብ ነው። የዚህ አይነቱ ልብ ሁሉም ጥቅም የሚገባው ለኔ ነው ብሎ በድፍረት ያስባል።**

"ንጉሡም አርጤክስስ ንግሥቲቱን አስቴርን፦ ይህን ያደርግ ዘንድ በልቡ የደፈረ ማን ነው? እርሱስ ወዴት ነው? ብሎ ተናገራት።"

አስቴር 7፡5

2. **ከንቀት ልብ ተጠንቀቅ። የንቀት ልብ ንቀት የተሞላ ልብ ነው። የዚህ አይቱ ልብ ያለው ሰው ሰዎችን ወደ ታች የሚመለከትና ስለሌሎች ያለው ግምት አነስተኛ ነው።**

"ትላለህም! እንዴት ትምህርትን ጠላሁ፥ ልቤም ዘለፋን ናቀ!"

ምሳሌ 5፡12

3. **በንቀት ከተሞላ ልብ ተጠንቀቅ። በንቀት የተሞላ ልብ ሌሎችን ያንኳስሳል። በርካታ የማያስደስቱ፣ አስደንጋጭና የሚያፀይፉ ነገሮችን የያዘ ነው።**

"በልቡ ሰባት ርኩሰት አለበትና በቃሉ አሳምሮ ቢናገርህ አትመነው።"

ምሳሌ 26፡25

4. ከክፉ ልብ ተጠንቀቅ፡፡ የዚህ አይነቱ ልብ በጭካኔ የተሞላና ለክፋት የተነሳሳ ልብ ነው፡፡

"ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ ፍልስጥኤማውያን በቂም ተነሣሥተው በክፉ ልብ ተበቅለዋልና፤ይሁዳንም በቆየ ጠላትነት ለማጥፋት ፈልገዋልና፤"

ሕዝቅኤል 25፡15 (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

5. ከአውሬነት ልብ ተጠንቀቅ፡፡ የአውሬነት ልብ ክፉና ከሰው የማይገጥም ተፈጥሮ ነው፡፡ ሰብአዊ ስሜት የሌላው ነው፡፡

"ልቡም ከሰው ልብ ይለወጥ፥የአውሬም ልብ ይሰጠው፤ ሰባት ዘመናትም ይለፉበት።"

ዳንኤል 4፡16

6. ከግፈኛ ልብ ተጠንቀቅ፡፡ ግፈኛ ልብ ፍትህ በማጓደልና በክፋት ይታወቃል፡፡ እመጽና ኃጢአት የሞላበት ልብ ነው፡ ፡

"እኔን ለማየት ቢገባ ከንቱነትን ይናገራል፤ ልቡ ኃጢአትን ሰበሰበለት፤ ወደ ሜዳ ይወጣል፤ ይናገራልም፡፡"

መዝሙር 41፡6

7. ከክፉ ልብ ተጠንቀቅ፡፡ ክፉ ልብ ለማታለል የተመደበ ልብ ነው፡፡ መጥፎና ሆን ብሎ ለሰዎች ጠንቅ የሚሆን ልብ ነው፡፡

በልባችሁ ክፋትን ታውጠነጥናላችሁ፤ በእጃችሁም ዐመፅን በምድር ላይ ትነዛላችሁ፡፡

8. በክፉ ከሚመኝ ልብ ተጠንቀቅ፡፡ በክፉ የሚመኝ ልብ የሌሎችን ነገር የመውሰድና የራሱ የማድረግ ብርቱ ምኞት አለ፡፡

"ምንዝር የሞላባቸው ኃጢአትንም የማይተዉ ዓይኖች አሉአቸው፤ የማይጸኑትን ነፍሳት ያታልላሉ፤ መመኘትን የለመደ ልብ አላቸው፤ የተረገሙ ናቸው።"

2ኛ ጴጥሮስ 2፡14

9. እግዚአብሔርን ከሚሳደብ ልብ ተጠንቀቅ። የዚህ አይነቱ ልብ ለተቀደሰ ነገር አክብሮት የሌለው ልብ ነው። በፀያፍ ቃላትና እርግማን የተሞላ ነው።

"ከልብ ክፉ አሳብ፥ መግደል፥ ምንዝርነት፥ ዝሙት፥ መስረቅ፥ በውሸት መመስከር፥ ስድብ ይወጣልና።"

ማቴዎስ 15፥19

10. ከግብዝ ልብ ተጠንቀቅ። ግብዝ ልብ የሌለውን በጎነት እንዳለው አድርጎ የሚያወራ ነው። የሌለውን ባህሪ፣ እምነት እና ስሜት ልክ እንዳለው አድርጎ ያስመስላል። የማስመሰል ልብ ነው።

"ዝንጉዎች ግን ቁጣን ያዘጋጃሉ፤ እርሱም ባሰራቸው ጊዜ አይጮኹም።"

ኢዮብ 36፥13

11. ከአታላይ ልብ ተጠንቀቅ። አታላይ ልብ ቅንነት የጎደለውና ውሸት የተሞላ ነው። መቼ እውነት እንደተናገረ መቼ ደግሞ ውሸት እንደተናገረ ፈጽሞ መለየት አይቻልም።

"ክፋትን በሚያውጠነጥኑ ሰዎች ልብ አታላይነት አለ፤ ሠላምን የሚያራምዱ ግን ደስታ አላቸው።"

ምሳሌ 12፥20

12. ከቀናተኛና አድመኛ ልብ ተጠንቀቅ። አድመኛ ልብ በክፋት የሌሎችን ስኬት አትብቆ ለራሱ የሚመኝ ልብ ነው።

"ነገር ግን መራራ ቅንዓትና አድመኛነት በልባችሁ ቢኖርባችሁ፥ አትመኩ፤ በእውነትም ላይ አትዋሹ።"

ያዕቆብ 3፥14

13. በክፋት ከተሞላ ልብ ተጠንቀቅ። አመጽና ተንኮል የተሞላ ልብ ነው። የከፍተኛ ጥፋትና አደጋ ምንጭ ነው።

"እግዚአብሔርም የሰው ክፋት በምድር ላይ እንደበዛ፥ የልቡ አሳብ ምኞትም ሁልጊዜ ፈጽሞ ክፉ እንደሆነ አየ።"

ዘፍጥረት 6፥5

14. ራሱን ከፍ ከፍ ከሚያደርግ ልብ ተጠንቀቅ። የዚህ አይነቱ ልብ በሆነው ወይም ባለው ነገር የሚኩራ ልብ ነው። የተነሳበትን የሚረሳ ልብ ነው። ከዝቅተኛ ስፍራ መነሳቱን የሚዘነጋ ልብ ነው።

"ልብህ እንዳይኳደድ… ከግብፅም ምድር ከባርነት ቤት ያወጣህን፥ …አምላክህን እግዚአብሔርን እንዳትረሳ…"

ዘዳግም 8፡14

"በትዕቢትና በልብ ኩራት… ዝግባን እንተካባቸዋለን የሚሉ በኤፍሬምና በሰማርያ የሚኖሩ ሕዝብ ሁሉ ያውቃሉ።"

ኢሳይያስ 9፡9

## ምዕራፍ 45

# አስተዋይ ልቦና ይኑርህ

አስተዋይ ልቦና ይኖርህ ዘንድ ጠንክረህ መስራት አለብህ። የእግዚአብሔርን ቃል የሚያሰላስልና መልካሙን ነገር የሚያስብ ልብ ለአገልግሎት በረከት የሚሆን ነው። በልብህ የምታስበው ነገር በምታደርገው ሁሉ ላይ ተጽዕኖ እንዳለው የታወቀ ነው።

1. የተሰበረ ልብ ይኑርህ። የተሰበረ ልብ የተናቀና ያልተሳካለት ልብ ነው። በጉዳት ያለፈ፣ የፈዘዘ፣ የተረበሸ፣ ትሁት እና የተጨቆነ ነው።

"እግዚአብሔር ልባቸው ለተሰበረ ቅርብ ነው፤ መንፈሳቸው የተሰበረውንም ያድናቸዋል።"

መዝሙር 34፡18

2. የሚያስተውል ልብ ይኑርህ። የሚስተውል ልብ ያለው ሰው ነገሮች እንዴት እንደሚከናወኑ ያውቃል። አስተዋይ ልብ ያለው ሰው ከምትናገረው ጥቂት ቃል ምን ለማለት እንደፈለግህ ይረዳል። የሌላው ስሜት ይገባዋል። የሚያስተውል ልብ ያለው ሰው ቸርና ይቅር ባይ ነው። ስህተት በሰራ ሰው ላይ አይፈርድም።

"ጆሮህ ጥበብን እንዲያደምጥ ታደርጋለህ፤ ልብህንም ወደ ማስተዋል ታዘነብላለህ።"

ምሳሌ 2፡2

3. ቃሉን የሚጠብቅ ልብ ይኑርህ። የዚህ አይነቱ ልብ የተነገረውን ቃል ይጠብቃል። የተሰበከለትን እያንዳንዱን ቃል የራሱ ከማድረጉም በላይ በእነርሱ ላይ ይጣበቃል። ቃሉን በውስጡ ጠብቆ የሚያኖር ልብ ለሌለው ሰው በማማከርና በስብከት ጊዜ ማጥፋት ከንቱ ነው።

"ያስተምረኝም ነበር፤ እንዲህም ይለኝ ነበር። ልብህ ቃሌን ይቀበል ትእዛዜን ጠብቅ፤ በሕይወትም ትኖራለህ።"

ምሳሌ 4፡4

4. **ስለሌሎች የሚጨነቅ ልብ ይኑርህ፡፡ የሚጨነቅ ልብ ሐዘንተኛ ነው፣በልብ ሕመም እረፍት በማጣት ይሰቃያል፡፡ የዚህ አይነቱ ልብ ያለው ሰው ልቡ የተሰበረና ሐዘንተኛ ነው፡፡**

"በብዙ መከራና ከልብ ጭንቀት በብዙም እንባ ጽፌላችሁ ነበርና፤ ይህም እናንተን አብዝቼ የምወድበትን ፍቅር እንድታውቁ እንጂ እንዳሳዝናችሁ አይደለም።"

2ኛ ቆሮንቶስ 2፡4

5. **ሸክም ያዘለ ልብ ይኑርህ፡፡ ሸክም ያዘለ ልብ ያለው ሰው ቁዘማ ያለበትና የዛለ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ እንዲህ ያሉ ሰዎች ከስታራ፣ድብቅና ውስብስብ ይመስላሉ፡፡**

"ለጥፋት ለቀረበው ሰው ብርቱ መጠጥ ስጡት፥ ነፍሱ ለመረረውም የወይን ጠጅ ስጡት፡፡"

ምሳሌ 31፡6

6. **ሐዘንተኛ ልብ ይኑርህ፡፡ የዚህ አይነቱ ልብ ደስታ የራቀው ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የዚህ አይነት ልብ ያለው ሰው ስቃይ የሚሰማው፣ የተጠቃና ሐዘንተኛ ሆኖ ይታያል፡፡ ሐዘንተኛ ልብ ያለውን ሰው ከውጭ አይቶ መለየት ቀላል ነው፡፡**

"በንጉሡ በአርጤክስስ በሀያኛው ዓመት በኒሳን ወር የወይን ጠጅ በፊቱ በነበረ ጊዜ ጠጁን አንሥቼ ለንጉሡ ሰጠሁት። ቀድሞ ግን በፊቱ ያለ ኃዘን እኖር ነበር። ንጉሡም፡ - ሳትታመም ፊትህ ለምን አዘነ? ይህ የልብ ኀዘን ነው እንጂ ሌላ ነገር አይደለም አለኝ። እጅግም ብዙ አድርጌ ፈራሁ። ንጉሡንም፡-ንጉሡ ሺህ ዓመት ይንገሥ፤ የአባቶቼ መቃብር ያለባት ከተማ ተፈትታለችና፥ በሮችዋም በእሳት ተቃጥለዋልና ፊቴ ስለምን አይዘን? አልሁት።"

ነህምያ 2፡1-3

7. **ነገሮችን የሚመረምር ልብ ይኑርህ፡፡ እንዲህ ያለው ልብ ነገሮችን በልቡ ያብሰለስላል፡፡ እያንዳንዱን ጉዳይ ዋጋ ሰጥቶ ይመዝናል፣ በጥልቀት ያጠናል፡፡**

"ማርያም ግን ይህን ነገር ሁሉ በልብዋ እያሰበች ትጠብቀው ነበር።"

ሉቃስ 2፡19

8. **ጥበበኛ ልብ ይኑርህ። የዚህ አይነቱ ልብ የሚታወቀው በምሁራዊ ዕውቀት ነው። ጥበበኛ ልብ እውነተኛ እና ትክክል የሆነውን የመመርመርና በሚገባ የመለየት ኃይል አለው። ጠቃሚ ስለሆኑ እውነታዎችና ሁኔታዎች መረጃ አለው። ብዙ ጊዜ እንዲህ ያሉት ሰዎች ብሩሕ አእምሮ ላቸው የተግባር ሰዎች ናቸው።**

"በአንጥረኛ፥ በብልህ ሠራተኛም፥ በሰማያዊና በሐምራዊ በቀይም ግምጃ በጥሩ በፍታም በሚሠራ ጠላፊ፥ በሸማኔም ሥራ የሚሠራውን፥ ማናቸውንም ሥራና በብልሃት የሚሠራውን ሁሉ ያደርጉ ዘንድ በእነርሱ ልብ ጥበብን ሞላ።"

ዘፀዓት 35፡35

# ምዕራፍ 46

# ግትር ልብን ተቃወም

አንዳንድ በጇ የማይሉ፣የማይማረኩ፣ እጅ የማይሰጡ፣ እሺ ወይ እምቢ የማይሉ፣መስማማት የማይሆንላቸው፣ አብረው የማይኀዙ፣ የማይገዙ ልቦች አሉ። ግትር (የማይታጠፍ) ልብ እንዳይኖርህ መከላከል ያስፈልግሀል። ያለ ትክክለኛ ልብ ለጌታ ብዙ ማከናወን አይቻልም። ልብህ የአገልግሎትህ ማዕከል በመሆኑ የምታደርገውን ነገር ውጤት ሁሉ ይወስናል።

1. **ንቅንቅ የማይልን ድንጋይ ልብ ተቃወም። ድንጋይ ልብ ምንም ርህራሄና ወዳጅነትን የማያሳይ ልብ ነው።**

"ልቡ እንደ ወፍጮ ድንጋይ የጠነከረ ስለሆነ፥ ፍርሀት የሚባል ነገር ከቶ አያውቅም።"
ኢዮብ 41፡24 (አዲሱ ትርጉም 1980)

2. **ወደኋላ የሚያፈገፍግን ልብ ተቃወም። የሚያፈገፍግ ልብ ወደተዋረደ ደረጃ የወረደ ልብ ነው። የሚያፈገፍግ ልብ ያለው ሰው እንደገባው ቃልና በተስማማው መሠረት ለማገልገል አይችልም።**

"ልባቸውን ከጽድቅ የሚመልሱ የእጃቸውን ሙሉ ዋጋ ይቀበላሉ፤ ደግ ሰውም ወሮታውን ያገኛል።"
ምሳሌ 14፡14 (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

3. **የስንፍና ልብን ተቃወም። የዚህ አይነቱ ልብ ስሜት የሌለው ፍርድ የሚያጣምም ነው።**

"የጠቢባን ከንፈር እውቀትን ትዘራለች፤ የሰነፎች ልብ ግን እንዲህ አይደለም።"
ምሳሌ 15፡7

4. **አሳች ልብን ተቃወም። የሚያስት ልብ ያለው ሰው ከትክክለኛው መስመር የወጣ ነው።**

"ያችን ትውልድ አርባ ዓመት ተቈጥቻት ነበር። ሁልጊዜ ልባቸው ይስታል፥ እነርሱም መንገዴን አላወቁም አልሁ።"
መዝሙር 95፡10

"ማርያም ግን ይህን ነገር ሁሉ በልብዋ እያሰበች ትጠብቀው ነበር።"

ሉቃስ 2፥19

8. ጥበበኛ ልብ ይኑርህ። የዚህ አይነቱ ልብ የሚታወቀው በምሁራዊ ዕውቀት ነው። ጥበበኛ ልብ እውነተኛ እና ትክክል የሆነውን የመመርመርና በሚገባ የመለየት ኃይል አለው። ጠቃሚ ስለሆኑ እውነታዎችና ሁኔታዎች መረጃ አለው። ብዙ ጊዜ እንዲህ ያሉት ሰዎች ብሩሕ አእምሮ ላቸው የተግባር ሰዎች ናቸው።

"በአንጥረኛ፥ በብልህ ሠራተኛም፥ በሰማያዊና በሐምራዊ በቀይም ግምጃ በጥሩ በፍታም በሚሠራ ጠላፊ፥ በሸማኔም ሥራ የሚሠራውን፥ ማናቸውንም ሥራና በብልሃት የሚሠራውን ሁሉ ያደርጉ ዘንድ በእነርሱ ልብ ጥበብን ሞላ።"

ዘፀዐት 35፥35

## ምዕራፍ 47

# ባለ ተስፋ ልብ ይኑርህ

በጎውን አሳቢ ሁን! ባለ ተስፋ ልብ ይኑርህ። ከእግዚአብሔር ታላላቅ ነገሮች ተጠባበቅ። ባለ ተስፋ ልብ እንዲኖርህ በርትተህ ሥራ። ተስፋ ባልተሞላ ልብ ለጌታ ብዙ ልትጠቀመው አትችልም።

1. **የሚያምን ልብ ይኑርህ። የሚያምን ልብ የእዚአብሔር ቃል እውነት እንደሆነ የሚያምንና የሚቀበል ልብ ነው። አግዚአብሔር ስመኖሩና ስለእግዚአብሄር መልካምነት ጽኑ መረዳት ያለው ልብ ነው።**

"ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ በአፍህ ብትመሰክር፣ እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤ ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መስከሮ ይድናልና።"

ሮሜ 10፡9-10

2. **ታማኝ ልብ ይኑርህ። ታማኝ ልብ የማይቀያየር፣ እምነት የሚጣልበት እና አስተማማኝ ልብ ነው። ታማኝ ልብ ስወዳጁና ስአጋሩ የታመነ ነው።**

"ልቡም በፊትህ የታመነ ሆኖ አገኘኸው፤ የከነዓናዊውንና የኬጢያዊውን፣ የአሞራዊውንም፣ የፌርዛዊውንም፣ የኢያቡሳዊውንም፣ የጌርጌሳዊውንም ምድር ለእርሱና ለዘሩ ትሰጥ ዘንድ ከእርሱ ጋር ቃልኪዳን አደረግህ አንተም ጻድቅ ነህና ቃልህን ፈጸምህ።"

ነህምያ 9፡8

3. **ጽኑ ልብ ይኑርህ። ጽኑ ልብ የማይለዋወጥ፣ የማይነቃነቅ ወይም የማይመለስ ልብ ነው።**

"እግዚአብሔር ሆይ ልቤ ጽኑ ነው፤ ልቤ ጽኑ ነው፤ እቀኛለሁ፤ እዘምራለሁ።"

መዝሙር 57፡7 (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

## 4. ዓላማ ያለው ልብ ይኑርህ፡፡ ዓላማ ያለው ልብ በውሳኔ የተሞላ ልብ ነው፡፡

"ዳንኤልም በንጉሡ መብልና በሚጠጣው ጠጅ እንዳይረክስ በልቡ አሰበ እንዳይረክስም የጃንደረቦቹን አለቃ ለመነ።"

ዳንኤል 1:8

## 5. የተደላደለ ልብ ይኑርህ፡፡ የተደላደለ ልብ በምንም ሁኔታ ውስጥ የሚረጋጋ ልብ ነው፡፡

"ልዩ ልዩ ዓይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ፤ ልባችሁ በጸጋ ቢጸና መልካም ነው እንጂ በመብል አይደለም፤ በዚህ የሚሠሩበት አልተጠቀሙምና።"

ዕብራውያን 13:9

# ክፍል አራት

# የአገልግሎት እውነታዎች

## ምዕራፍ 48

# አገልግሎትህን ማስፋት የምትችልበት መንገድ

አገልግሎትህን ማስፋት ትችላለህ። የምታደርገው ነገር ወደ ሌላ ምዕራፍ ማሻገር ትችላለህ። እግዚአብሔር በብዙ ህዝብ ፊት እንድትሰብክ ሊያደርግህ ይችላል። እጅግ ብዙ ህዝብ ሊሰጥህ ይችላል። ትልቅ ህንጻና ብዙ አባላትን ሊሰጥህ ይችላል። ይህ መስፋፋት ግን የሚመጣው እንዴት ነው? በህይወትህ እና በአገልግሎትህ ዕድገትን የሚያመጡ ሰባት እርምጃዎችን ላካፍልህ እወዳለሁ።

## አገልግሎትህን ለማስፋት የሚያስችሉ ሰባት እርምጃዎች

### 1. ልብህን አስፋ።

"በዚያን ጊዜ የባሕሩ በረከት ወደ አንቺ ስለሚመለስ፥ የአሕዛብም ብልጥግና ወደ አንቺ ስለሚመጣ፥ አይተሽ ደስ ይልሻል፥ ልብሽም ይደነቃል፤ ይሰፋማል።"

ኢሳይያስ 60፡5

"እናንተ የቆሮንቶስ ሰዎች ሆይ፥ አፋችን ለእናንተ ተከፍቶአል፤ ልባችንም ሰፍቶላችኋል፤"

2ኛ ቆሮንቶስ 6፡11

የስራህ ሥፋት በልብህ ስፋት መጠን ነው። ከጥቂት አመታት በፊት እግዚአብሔር ልቤን በጋና ህዝብ ፍቅር ሞላው። በአንድ ወቅት ለጋና ህዝብ ለየት ያለ የሞቀ ፍቅር ይሰማኝ ጀመር። አገልግሎቴ የጋናን ህዝብ ይደርስ ዘንደ እግዚአብሔር ልቤን አሰፋልኝ።

በአገልግሎቴ ሌላ ወቅት ደግሞ ጋናውያን ላልሆኑ ሰዎች የተለየ ፍቅር አደረብኝ። አሁን ደግሞ እንደገና እግዚአብሔር ከጋና ውጭ ያለውን ህብረተሰብ እንዳገለግል ልቤን አሰፋልኝ ማለት ነው። ወዲያውኑ ጋናውያን ያልሆኑ ሰዎች በአገልግሎቴ መሳብ ጀመሩ። እግዚአብሔር ልብህን ካላሰፋልህ ወደዚህ አይነቱ አገልግት ለመግባት አትችልም።

## 2. እርምጃህን አስፋ።

"አረማመዴን በበታቼ አሰፋህ፥ እግሮቼም አልተንሸራተቱም።"

2ኛ ሳሙኤል 22:37

አገልግሎትህን ለማስፋት እርምጃህን ማስፋት አለብህ። ይህ ማለት ከእግዚአብሔር ጋር አረማመድህን አስፋ ማለት ነው። የበለጠ ለመስራት ከፈለግህ ወደ እግዚአብሔር ይበልጥ ጠለቅ ማለት አለብህ፡ ፡ አገልግትህ እስኪሰፋ ድረስ የበለጠ መጸለይ፣የበለጠ ቃሉን ማንበብ፣ የበለጠ የካሴት መልዕክቶችን ማዳመጥ በመልዕክቶች መጥለቅለቅ አለብህ።

## 3. የእምነት ቃልህን አስፋ።

"ሐናም ስትጸልይ እንዲህ አለች። ልቤ በእግዚአብሔር ጸና፥ ቀንዴ በእግዚአብሔር ከፍ ከፍ አለ፤ አፌ በጠላቶቼ ላይ ተከፈተ፤ በማዳንህ ደስ ብሎኛል።"

1ኛ ሳሙኤል 2:1

አገልግሎትህን ለማስፋት የምታናገረውን የእምነት ቃል ማስፋት አለብህ። ቀደም ሲል ትናገራቸው ከነበሩት ይልቅ ታላላቅ ነገሮችን መናገር አለብህ። ስለአገልግሎትህ የምትናገረውን መቀየር አለብህ። አገልገሎትህ የሰፋና የተባረከ እንደሆነ መናገር አለብህ።

ስለ አባላቶችህ፣ ስለመጋቢዎችና ስለረዳቶችህ መልካም ነገር መናገር አለብህ። የምትናገረው ታላቅ የእምነት ቃል ወደ ታላቅ አገልግሎት ይመራሀል። በአንድ ወቅት የቤተክርስቲያኔን ስም መለውጥ ነበረብኝ ምክንያቱም የቀድሞ ስም የሚገድብ አይነት ትርጉም ስለነበረው ነበር። የእምነት ቃሌን በማሳደግ ለአገልግሎቴ አለምአቀፋዊ ስም ሰጠሁት። በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ይህ የሰፋ የእምነት ቃል ወደ ሰፋ አገልግሎት መራኝ።

የሰፋው የእምነት ቃልህ ለተቀበልከው ታላቅ ራዕይ ማስረጃ ነው። ይህ ታላቅ ራዕይ ወደ ሰፊ አገልግሎት ይመራል።

"ራእይ ባይኖር ሕዝብ መረን ይሆናል ሕግን የሚጠብቅ ግን የተመሰገነ ነው።"

ምሳሌ 29:18

## 4. የአገልግሎትህን አድማስ አስፋ።

"በሌሎች ድካም ያለልክ አንመካም፥ ነገር ግን እምነታችሁ ሲያድግ ከእናንተ ወዲያ ባለው አገር እስከንሰብክ ሥራችንን እየጨመርን፥ በክፍላችን በእናንተ ዘንድ እንድንከብር ተስፋ እናደርጋለን፤ በሌላው ክፍል ስለተዘጋጀው ነገር አንመካም።"

2ኛ ቆሮንቶስ 10፡15-16

ብዙ ሰዎች የተወሰነ የአግልግሎት መስመር ነው ያላቸው። ምናልባት መጋቢ ትሆንና በማስተማሩ ረገድ እምብዛም ትሆናለህ። ምናልባት ደግሞ አስተማሪ ትሆንና ትንቢታዊ አገልግሎት ላይ እጅግም ልትሆን ትችላለህ። አልተሰጠህም ይሆናል። አገልግትህን ለማስፋት ስትንቀው የነበረውን ጨምሮ በሁሉም የአገልግሎት መስክ ደፍረህ መግባት አለብህ።

በአገልግሎቴ እየደግሁ ስሄድ በተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች እየገባሁ እንደሆንኩ ተረዳሁ።

መጽሐፍ በመጻፍ፣ በሚሲዮናዊነት፣ ከዚያም ወደ ወንጌል ማዳረስ አገልግሎት ገባሁ። እነዚህ ሁሉ ለኔ አዳዲስ የአገልግሎት መስኮች ነበሩ። ደረጃ በደረጃ እያንዳንዱ የአገልግሎት ዘርፍ እድገትን ወደ አገልግሎቴ አመጣ። ወደተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች በመዘርጋት መስፋት ይመጣል።

## 5. ድንበርህን አስፋ።

"አሕዛብን ከፊትህ አወጣለሁ፥ አገርህንም አሰፋለሁ፤ በአምላክህም በእግዚአብሔር ፊት ለመታየት በዓመት ሦስት ጊዜ ስትወጣ ማንም ምድርህን አይመኝም።"

ዘፀአት 34፡24

"አምላክህ እግዚአብሔር እንደነገረህ አገርህን ባሰፋ ጊዜ፥ ሰውነትህም ሥጋ መብላት ስለወደደች ሥጋ ልብላ ስትል፥ እንደ ሰውነትህ ፈቃድ ሥጋን ብላ።"

ዘዳግም 12፡20

ድንበርህን ማስፋት ማለት ካለህበት መልክአምድራዊ ድንበር አልፈህ መሄድ ማለት ነው። አንዳንድ አገልግሎቶች ለአንድ የህብረተሰብ ክፍል ብቻ ፣ አንዳንዶች ለከተማ አገልግሎት ብቻ፣ አንዳንዶች ደግሞ ለተወሰነ ህዝብ ራሳቸውን ይወስናሉ። አንዳንድ አገልጋዮች ደግሞ አህጉራዊ ብሎም አለምአቀፋዊ ናቸው። ቤተክርስቲያናችን ኮርሌ ቡ ክርስቲያን ሴንተር የሚል ስም ነበረው። ነገር ግን እግዚአብሔር ለሰፋ አገልግሎት እንደጠራኝ ስለገባኝ ስሙ ለኮርሌ ቡ ህዝብ ብቻ ወስኖ እንዳያስቀረኝ እሰጋ ነበር።

እግዚአብሔር ደግሞ ሰፋ ያለ አገልግሎት እየሰጠኝ እንደሆነ ይሰማኝ ነበር፡፡ በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ አገልግሎቱ ከማህበረሰብ ወደ አለም አቀፋዊ አገልግሎት አደገ፡፡

## *6. ግዛትህን አስፋ፡፡*

**"ያቤጽም እባክህ፥ መባረክን ባርከኝ፥ አገሬንም አስፋው፤ እጅህም ከእኔ ጋር ትሁን፤ እንዳያሳዝነኝም ከክፉት ጠብቀኝ ብሎ የእስራኤልን አምላክ ጠራ፤ እግዚአብሔርም የለመነውን ሰጠው፡፡"**

**1ኛ ዜና መዋዕል 4:10**

የግዛትህ መስፋት መባረክ ነው፡፡ ግዛትህን ማስፋት ማለት የተጽዕኖ ክልልህን ማስፋት ማለት ነው፡፡ በአንዳንድ ቦታዎች ቢሮዎች ላይኖርህ ይችላል ነገር ግን እግዚአብሔር ተጽዕኖ የምታመጣበት ግዛት አድርጎ ሰጥቶህ ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ ኬኔት ሀገን ወደ ምዕራብ አፍሪካ መጥተው አያውቁም፡፡ ነገር ግን አገልግሎታቸው በዚያ ባሉ አገሮች ላይ ከፍጸኛ ተጽዕኖ አድርጓል፡፡

## *7. መኖሪያህን አስፋ፡፡*

**"የድንኳንሽን ስፍራ አስፊ፥ መጋረጃዎችሽንም ይዘርጉ፤ አትቆጥቢ፤ አውታሮችሽን አስረዝሚ፤ ካስሞችሽንም አጽኚ፡፡"**

**ኢሳይያስ 54:2**

መኖሪያህን ማስፋት የሚያመለክተው ድንኳንህን የምትተክልበትን መሬት ማስፋትን ነው፡፡ ከላይ ያነበብነው ጥቅስ ድንኳኑ ይሰፋ ዘንድ አውታሮችን ካስሞችን የማጽናት ትዕዛዝን ይገልጣል፡፡ በመሠረቱ መኖሪያን ማስፋት የሚናገረው ለአገልግሎት የምታደርገውን ዝግጅት ነው፡፡

ዝግጅት በየትኛውም አገልግሎት ውጤት ላይ ትልቅ ሚና አለው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ መጥምቁ ዮሐንስ ያሉ ፋና ወጊዎች ቅድመ ዝግጅቱን ሳያደርጉለት ዘሎ ወደ አገለግሎት አልገባም፡፡ ከዚያም በተጨማሪ በፊቱ መንገድን ይጠርጉ ዘንድ ሰባ ሰዎችን ልኳል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በ‹‹ዝግጅት›› በሚገባ ያምናል፡፡

ለስብከትና ለትምህርት የምታደርገው ዝግጅት በጨመረ ቁጥር ውጤቱ በአገልግሎህ ላይ መንጸባረቅ ይጀምራል፡፡ ያለፍሬ የሚቀር ጥረት አይኖርም!

የጀማ ወንጌል ስብከት አገልግሎት ስለ ሰፊ የዝግጅት ጥረት መነሻ ልምድ ሰጥቶኛል፡፡ ጠለቅ ያለና ጊዜ የወሰደ ዝግጅት አድርሰገን በምናዘጋጃቸው ክሩሴዶች ላይ የሚገኙት ሰዎች ቁጥር በአስደናቂ ሁኔታ መጨመሩን አስተዋልኩ፡፡ ሰዎች ተባርከው በሚያስገርም ሁኔታ ያሸበሽባሉ፡፡ ቢሊግራሃም በአንድ ክሩሴድ ላይ ከማገልገላቸው በፊት ለሁለት ዓመት ዝግጅት እንደሚያደርጉ በሰማሁ ጊዜ ዝግጅት በየትኛውም አገልግሎት ላይ ያለውን ሚና በሚገባ ተረዳሁ፡፡

## ምዕራፍ 49

# እረኛ ብርሃን ነው

"እግዚአብሔርም ሁለት ታላላቆች ብርሃናትን አደረገ ትልቁ ብርሃን በቀን እንዲሠለጥን፥ ትንሹም ብርሃን በሌሊት እንዲሰለጥን ከዋክብትንም ደግሞ አደረገ"

ዘፍጥረት 1፥16

እግዚአብሔር ሁለት ዓይነት ብርሃናትን ፈጠረ። ትንሽና ትልቅ ብርሀን። እነዚህ ብርሀናት በቀንና በሌሊት የሚሰለጥኑ ናቸው። በአገልግሎትም ትንሽና ትልቅ ብርሀናት አሉ። እግዚአብሔር የወንጌልን ብርሃን ለዓለም ለማብራት ትልቅና ትንሽ ብርሀን አጥሯል። አንዳንድ አገልጋዮች ‹‹ታላላቅ›› ብርሃናት ሲሆኑ አንዳንዶች ደግሞ ‹‹ትንንሽ›› ብርሀናት ናቸው።

አገልግሎት በብርሀን ተመስሏል። ኢየሱስ በተደጋጋሚ ራሱን በብርሀን ይመስል ነበር። ደቀመዛሙርቱም ብርሀን ሆነው እንዲያበሩ ያሳስባቸው ነበር። የኢየሱስ ደቀመዛሙርት ብርሀን ለመሆን ወደ ዓለም ሁሉ ወጡ።

## 1. ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ አለም የሚያበራ ታላቅ ብርሀን ነው። በወንጌላት ውስጥ በተደጋጋሚ እረሱ ወደ አለም የመጣ ብርሀን እንደሆነ ተናግሯል።

"ናዝሬትንም ትቶ በዛብሎንና በንፍታሌም አገር በባሕር አጠገብ ወደአለችው ወደቅፍርናሆም መጥቶ ኖረ። በነቢዩም በኢሳይያስ፡- የዛብሎን ምድርና የንፍታሌም ምድር፥ የባሕር መንገድ፥ በዮርዳኖስ ማዶ፥ የአሕዛብ ገሊላ፤ በጨለማ የተቀመጠው ሕዝብ ታላቅ ብርሃን አየ፥ በሞት አገርና ጥላ ለተቀመጡትም ብርሃን ወጣላቸው የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሆነ።"

ማቴዎስ 4፥13-16

"በእርሱ ሕይወት ነበረች፥ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች። ብርሃንም በጨለማ ይበራል፥ ጨለማም አላሸነፈውም።"

ዮሐንስ 1፥4-5

"ሁሉ በእርሱ በኩል እንዲያምኑ ይህ ስለ ብርሃን ይመሰክር ዘንድ ለምስክር መጣ። ስለ ብርሃን ሊመሰክር መጣ እንጂ፥ እርሱ ብርሃን አልነበረም። ለሰው ሁሉ የሚያበራው እውነተኛው ብርሃን ወደ ዓለም ይመጣ ነበር።"

ዮሐንስ 1፡7-9

"ብርሃንም ወደ ዓለም ስለመጣ ሰዎችም ሥራቸው ክፉ ነበርና ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ስለወደዱ ፍርዱ ይህ ነው።"

ዮሐንስ 3፡19

"ደግሞም ኢየሱስ፦ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም ብሎ ተናገራቸው።"

ዮሐንስ 8፡12

"በዓለም ሳለሁ የዓለም ብርሃን ነኝ።"

ዮሐንስ 9፡5

"ኢየሱስም፦ ገና ጥቂት ጊዜ ብርሃን ከእናንተ ጋር ነው። ጨለማ እንዳይደርስባችሁ ብርሃን ሳለላችሁ ተመላለሱ፤ በጨለማም የሚመላለስ ወዴት እንዲሄድ አያውቅም።

የብርሃን ልጆች እንድትሆኑ ብርሃን ሳለላችሁ በብርሃኑ እመኑ አላቸው። ኢየሱስም ይህን ተናግሮ ሄደና ተሰወረባቸው።"

ዮሐንስ 12፡35-36

"ኢየሱስም ጮኸ፥ እንዲህም አለ፦ በእኔ የሚያምን በላከኝ ማመኑ ነው እንጂ በእኔ አይደለም፤ እኔንም የሚያይ የላከኝን ያያል። በእኔ የሚያምን ሁሉ በጨለማ እንዳይኖር እኔ ብርሃን ሆኜ ወደ ዓለም መጥቻለሁ።"

ዮሐንስ 12፡44-46

## 2. መጥምቁ ዮሐንስም እንደብርሀን ተገልጾአል፡፡

"ስለ ብርሃን ሊመሰክር መጣ እንጂ፥ እርሱ ብርሃን አልነበረም።"

ዮሐንስ 1፡8

"እርሱ የሚነድና የሚያበራ መብራት ነበረ፥ እናንተም ጥቂት ዘመን በብርሃኑ ደስ ሊላችሁ ወደዳችሁ።"

ዮሐንስ 5፡35

## 3. እያንዳንዱ አገልጋይ ለዓለም ብርሀንን የሚሰጥ የሚነድ ሻማ ነው፡፡ አገልግሎትህ በዓለም ጨለማ የሚገልጥ ብርሀን ነው፡፡

"መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ።"

ማቴዎስ 5፥16

"ስለመላእክትም መላእክቱን መናፍስት አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል የሚያደርግ..."

ዕብራውያን 1፥7

## ምዕራፍ 50

# አንዳንድ ሰዎች ለምንድነው ትልቅ ብርሀን የሚሆኑት?

## አንዳንድ ሰዎች ትልቅ ብርሀን የሚሆኑባቸው አራት ምክንያቶች

### 1. የእግዚአብሔር ሉአላዊ ውሳኔ አንዳንዶች ትልልቅ ብርሀን እንዲሆኑ ያደርጋል።

"ለአምላክህ ለእግዚአብሔር አንተ ቅዱስ ሕዝብ ነህና በምድር ፊት ከሚኖሩ አሕዛብ ሁሉ ይልቅ ለእርሱ ለራሱ ሕዝብ ትሆንለት ዘንድ አምላክህ እግዚአብሔር መረጠህ።"

ዘዳግም 7፡6

"ብቻ እግዚአብሔር ስለ አባቶችህ ደስ ብሎታል፥ እነርሱንም ወድዶአል፤ ከእነርሱም በኋላ እናንተን ዘራቸውን እንደዛሬው ሁሉ ከአሕዛብ ሁሉ መካከል መረጠ።"

ዘዳግም 10፡15

"ለእግዚአብሔር አንተ ቅዱስ ሕዝብ ነህና፥ በምድርም ላይ ከሚኖሩ አሕዛብ ሁሉ ይልቅ ለእርሱ ለራሱ ሕዝብ ትሆንለት ዘንድ እግዚአብሔር አንተን መርጦአልና።"

ዘዳግም 14፡2

### 2. የእግዚአብሔር ጸጋ አንዳንዶችን ትልቅ ብርሀን ያደርጋቸዋል።

"ተመልሼም ከተራራው ወረድሁ፥ ጽላቶችንም በሠራሁት ታቦት ውስጥ አደረግኋቸው፤ እግዚአብሔርም እንዳዘዘኝ በዚያ ኖሩ።"

ዘዳግም 10፡15

"ወደ ንጉሡም ትገባ ዘንድ የመርዶክዮስ አጎት የአቢካኢል ልጅ የአስቴር ተራ በደረሰ ጊዜ የሴቶች ጠባቂው የንጉሡ ጃንደረባ ሄጌ ከሚለው በቀር ምንም አልፈለገችም ነበር። አስቴርም በሚያዩአት ሁሉ ዓይን ሞገስ አግኝታ ነበርና። አርጤክስስም በነገሠ በሰባተኛው ዓመት አዳር በሚባለው በአሥራ ሁለተኛው ወር አስቴር ወደ ንጉሡ ቤት ተወሰደች። ንጉሡም ከሴቶች ሁሉ ይልቅ አስቴርን ወደደ፥ በዓይኑም ከደናግል ሁሉ ይልቅ ሞገስንና መወደድን አገኘች፤ የመንግሥቱንም ዘውድ በራስዋ ላይ አደረገ፥ በአስጢንም ፋንታ አነገሣት።"

አስቴር 2፡15-17

## 3. ከአንድ በላይ ስጦታ ወይም መክሊት በመቀበላቸው አንዳንዶች ትልቅ ብርሀን ያደርጋቸዋል።

"ለእያንዳንዱ እንደ ዓቅሙ፥ ለአንዱ አምስት መክሊት ለአንዱ ሁለት ለአንዱም አንድ ሰጠና ወደ ሌላ አገር ወዲያው ሄደ።"

ማቴዎስ 25፡15

"እስራኤልም ዮሴፍን እነሆ እኔ እሞታለሁ እግዚአብሔርም ከእናንተ ጋር ይሆናል፥ ወደ አባቶቻችሁም ምድር ይመልሳችኋል። እኔም ከአሞራውያን በሰይፌና በቀስቴ የወሰድሁትን ለአንተ ከወንድሞችህ አንድ እጅ አብልጬ ሰጠሁህ አለው።"

ዘፍጥረት 48፡21-22

## 4. የአባት ምርቃት አንዳንዶችን ትልቅ ብርሀን ያደርጋቸዋል።

ሴም፣ ካምና ያፌት ከአባታቸው ባገኙት ምርቃት መለያየት ምክንያት በዚህ አለም ላይ የሆነላቸው ነገር የተለያየ ነበር። በእርግጥም የአባት ምርቃት በአገልግሎትህ ላይ ድርሻ አለው። ይህ ትልቅ ወይም ትንሽ ብርሀን መሆንህን ይወስናል። ከመንፈሳዊ አባትህ ትልቅ ምርቃት ለማግኘት መጣር አለብህ። በምንም አይነት አባትህ እንዳይረግምህ መጠንቀቅ አለብህ። ከአባትህ ያገኘኸው ምርቃት ታላቅ ከሆነ ከህይወት የሚወጣው ብርሀን ይጨምራል።

ዮሴፍ ከቀደሙት አባቶቹ ይልቅ ከአባቱ ምርቃትን እንዳገኘ ታስተውላለህ። ይህም ትልቅ ምርቃት ትልቅ ብርሀን እንዲሆን አድርጎታል። « የአባትህ በረከቶች ጽኑዓን ከሆኑ ከተራሮች በረከቶች ይልቅ ኃያላን ናቸው ዘላለማውያን ከሆኑ ከኮረፍቶችም በረከቶች ይልቅ ኃያላን ናቸው እነርሱም በዮሴፍ ራስ ላይ ይሆናሉ፥በወንድሞቹ መካከል አለቃ በሆነው ራስ አናት ላይ።፡» (ዘፍጥረት 49፡26)

"እንዲህም አለ፡- ከነዓን ርጉም ይሁን ለወንድሞቹም የባሪያዎች ባሪያ ይሁን። እንዲህም አለ፡- የሴም አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ፥ ከነዓንም ለእነርሱ ባሪያ ይሁን። እግዚአብሔርም ያፌትን ያስፋ፥ በሴምም ድንኳን ይደር፤ ከነዓንም ለእነርሱ ባሪያ ይሁን።"

ዘፍጥረት 9፡ 25-27

## ምዕራፍ 51

# ትልቅ ብርሀን ልትሆን የምትችልበት መንገድ

1. መታዘዝ ትልቅ ብርሀን ያደርግሀል።

"አሁንም ቃሌን በእውነት ብትሰሙ ኪዳኔንም ብትጠብቁ፥ ምድር ሁሉ የእኔ ናትና ከአሕዛብ ሁሉ የተመረጠ ርስት ትሆኑልኛላችሁ።"

ዘጸአት 19፥5

"አሁንም ቃሌን በእውነት ብትሰሙ ኪዳኔንም ብትጠብቁ፥ ምድር ሁሉ የእኔ ናትና ከአሕዛብ ሁሉ የተመረጠ ርስት ትሆኑልኛላችሁ። ይወድድሀማል፥ ይባርክሀማል፥ ያበዛሀማል። ይሰጥሀም ዘንድ ለአባቶችህ በማለላቸው ምድር የሆድህን ፍሬ የመሬትህንም ፍሬ፥ እህልህን ወይንህንም ዘይትህንም፥ የከብትህንም ብዛት የበግህንም መንጋ ይባርክልሃል። ከአሕዛብም ሁሉ ይልቅ የተባረክህ ትሆናለህ፤ በሰውህና በከብትህም ዘንድ ወንድ ቢሆን ወይም ሴት ብትሆን መካን አይሆንብህም። እግዚአብሔርም ሕማምን ሁሉ ከአንተ ያርቃል፤ የምታውቀውንም ክፉውን የግብፅ በሽታ ሁሉ በአንተ ላይ አያደርስብህም፥ በጠላቶችህም ሁሉ ላይ ያመጣባቸዋል።"

ዘዳግም 7፥12-15

2. ትህትና ትልቅ ብርሀን ያደርግሀል።

"ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳል፥ ራሱንም የሚያዋርድ ሁሉ ከፍ ይላል።"

ማቴዎስ 23፥12

3. ልቀት ትልቅ ብርሀን ያደርግሀል። በምታደርገው ሁሉ ልቀህ መገኘት ወደ እድገት ይመራሀል። ቡቱቶን፣ ንጹህ ያልሆነውን፣ እድፋም ነገሮችን ማስወገድ ወደ ዕድገት ይመራል።

"ዳንኤልም መልካም መንፈስ ስላለው ከአለቆችና ከመሳፍንት በለጠ፤ ንጉሡም በመንግሥቱ ሁሉ ላይ ይሾመው ዘንድ አሰበ።"

ዳንኤል 6፥3

4. ጽድቅ ትልቅ ብርሀን ያደርግሀል። አመፃን መጥላት ሳቅ ያልክ ብርሀን ያደርግሀል።

"ጽድቅን ወደድህ ዓመፅንም ጠላህ፤ ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክህ ከጓደኞችህ ይልቅ በደስታ ዘይት ቀባህ።"

ዕብራውያን 1፥9

5. በደህንነትህ መደሰት ትልቅ ብርሀን ያደርግሀል። በደህንነት ላይ ትኩረት ማድረግ፣ ደህንነትን መረዳትና ስለደህንነት መስበክ ትልቅ ብርሀን ያደርግሀል።

ዛሬ ብዙ ሰዎች በደህንነት ላይ ትኩረት አያደርጉም። ምክንያቱም እንደመጀመሪያ ትምህርት ስለሚቆጥሩት ነው። ደህንነት ከእግዚአብሔር ከምንቀበለው ከየትኛውም በረከት የሚልቅ ታላቅ በረከት ነው። ደህንነታችንን መረዳት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችን ዋና ትኩረት መሆን አለበት። ደህንነታችንን መረዳት አመስጋኞችና ፍሬአማዎች ያደርጉናል።

"ሐናም ስትጸልይ እንዲህ አለች፤ ልቤ በእግዚአብሔር ጸና፥ ቀንዶ በእግዚአብሔር ከፍ ከፍ አለ፤ አፌ በጠላቶቼ ላይ ተከፈተ፤ በማዳንህ ደስ ብሎኛል።"

1ኛ ሳሙኤል 2፡1

6. ያሳድግህ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ብትመለከት ትልቅ ብርሀን ያደርግሀል። ትልቅ ብርሀን ለመሆን ወደ ምስራቅ፣ ወደ ምዕራብ፣ ወደ ደቡብ ፣ ወይም ወደ ሰሜን መመልከት ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ መመልከት ነው። ወደ ሰዎች አትመልከት። ታላቅ መሆን የሚመጣው ከእግዚአብሔር ብቻ ነው።

"ከብር ከምሥራቅ ወይም ከምዕራብ ወይም ከምድረ በዳ የለምና።"

መዝሙር 75፡6

## ምዕራፍ 52

# የአገልግሎት መንፈሳዊ ጅማቶች

"ከእርሱም የተነሣ አካል ሁሉ እያንዳንዱ ክፍል በልክ እንደሚሠራ፥ በተሰጠለት በጅማት ሁሉ እየተጋጠመና እየተያያዘ፥ ራሱን በፍቅር ለማነጽ አካሉን ያሳድጋል።"

ኤፌሶን 4፡16

አሁን ወደ ብስለት የምንደርስበትና ለሌሎች ድርሻ እውቅና የምንሰጥበት ጊዜ ነው። እጅ ግንደ አካል ያስፈልገዋል፤ ምክንያቱም ደረት ልብን ተሸክሟል። ግንደ አካል ደግሞ እጅ ያስፈልገዋል፤ ምክንያቱም ሆድ ምግብ ከጠረጴዛ ላይ አንስቶ መመገብ አይችልም። በመጠኑ ለመረዳት ይህ ምሳሌያዊ አገላለጽ በቂ ነው። ያም ሆኖ ግን እኛ በየጊዜው ይህን መርሆ በህይወታችን ስንተላለፍ እንገኛለን።

ከታላላቅ የአገልግሎት ምስጢራት አንዱ በክርስቶስ አካል ውስጥ ያለው የመንፈሳዊ ጅማቶች ምስጢር ነው። በጅማቶች አማካኝነት ከተቀረው የክርስቶስ አካል ጋር ተጋጥመሀል። በጅማቶች አማካኝነት ለእድገትህ ከሚጠቅሙህ ሰዎች ጋር ተጋጥመሀል። በጅማቶች አማካኝነት ለውጠታማ አገልግሎት የሚያስፈልግህን ታገኛለህ።

ብዙ ጊዜ ካንተ በጣም ከሚለይ ነገር ጋር ትገናኛለህ። ግንደ አካል ከእጅና ከክንድ ጋር ሲነጻጸር ምን ያህል ትልቅ እንደሆነ አስብ። ያም ሆኖ ግን ትልቁ ግንደ አካል ደስተኛና ፍሬያማ ለመሆን ቀጠን ካለው ክንድ ጋር መጋጠም ያስፈልገዋል።

በቀላሉ ለመጋጠም የሚያስችል ጤናማ ጅማትን ማግኘት ለመቀባት፣ ለመጠበቅ እና ለመንፈሳዊ ምሪት በጣም አስፈላጊ ነው። በመንፈሳዊ ጅማት ስለመጋጠም ታላላቅ ምሳሌዎች አንዱ በኤልያስና በኤልሳዕ መካከል የነበረው መንፈሳዊ መጋጠም ነበር። ይህ መጋጠም በኤልያስ ላይ የነበረው ቅባት ወደ ኤልሳዕ ህይወት በእጥፍ የተላለፈበት መንፈሳዊ መጋጠም ነው። ኤልሳዕ የእግዚአብሔርን ጸጋ በእጥፍ የተቀበለው ከኤልያስ ጋር ተጣብቆ ስለነበረ ነው። ያን በሁሉም አንጻር አስፈላጊ የሆነ መጋጠም ምንም እንዲነካው አልፈቀደም።

# በኤልያስና በኤልሳዕ መካከል ስለነበረው በመንፈሳዊ ጅማት መጋጠም አሥር መገለጦች

1. ኤልያስ እንኳ ከእርሱ እንዲለይ ሊያደርገው እስከማይችል ድረስ ኤልሳዕ ከኤልያስ ጋር ተጣብቆ ነበር፡፡ ኤልያስ እንኳ የሰጠው ምክር ኤልሳዕ ለኤልያስ ካለው ፍቅርና መሰጠት ጋር የሚጋጭ ነበር፡፡ ኤልሳዕ ከኤልያስ መለየት ሊያገኝ ከሚፈልገው ነገር መለየት እንደሆነ ገብቶታል፡፡

"ኤልያስም ኤልሳዕን፦ እግዚአብሔር ወደ ቤቴል ልኮኛልና በዚህ ቆይ አለው። ኤልሳዕም ሕያው እግዚአብሔርን! በሕያው ነፍስህም እምላለሁ፥ አልለይህም አለ። ወደ ቤቴልም ወረዱ።"

2ኛ ነገሥት 2፡2

2. ሕያው እግዚአብሔርን ብሎ እስከመማል ድረስ ኤልሳዕ ከኤልያስ ላለመለየት ቆርጦ ነበር፡፡

"ኤልያስም ኤልሳዕን፦ እግዚአብሔር ወደ ቤቴል ልኮኛልና በዚህ ቆይ አለው። ኤልሳዕም ሕያው እግዚአብሔርን! በሕያው ነፍስህም እምላለሁ፥ አልለይህም አለ። ወደ ቤቴልም ወረዱ።"

2ኛ ነገሥት 2፡2

3. በኤልያስ ነፍስ እስከመማል ድረስ ኤልሳዕ ከኤልያስ ላለመለየት ቆርጦ ነበር፡፡

"ኤልያስም ኤልሳዕን፦ እግዚአብሔር ወደ ቤቴል ልኮኛልና በዚህ ቆይ አለው። ኤልሳዕም ሕያው እግዚአብሔርን! በሕያው ነፍስህም እምላለሁ፥ አልለይህም አለ። ወደ ቤቴልም ወረዱ።"

2ኛ ነገሥት 2፡2

4. ሃምሳ ነቢያት ሊለዩት እስከማይችሉ ድረስ ኤልሳዕ ከኤልያስ ጋር ተጣብቆ ነበር፡፡ ብዙዎች ሐሰተኛ ነቢያትን አምነው ጠፍተዋል፡፡

"በቤቴልም የነበሩ የነቢያት ልጆች ወደ ኤልሳዕ ወጥተው እግዚአብሔር ጌታህን ከራስህ ላይ ዛሬ እንዲወስደው አውቀሃልን? አሉት። እርሱም፦ አዎን፥ አውቄአለሁ ዝም በሉ አላቸው።"

2ኛ ነገሥት 2፡3

5. በጌልጌላ ያጋጠመው ሁኔታ ሊለየው እስከማይችል ድረስ ኤልሳዕ ከኤልያስ ጋር ተጣብቆ ነበር።

"እንዲህም ሆነ፤ እግዚአብሔር ኤልያስን በዐውሎ ነፋስ ወደ ሰማይ ሊያወጣው በወደደ ጊዜ ኤልያስ ከኤልሳዕ ጋር ከጌልገላ ተነሣ። ኤልያስም ኤልሳዕን፦ እግዚአብሔር ወደ ቤቴል ልኮኛልና በዚህ ቆይ አለው። ኤልሳዕም ሕያው እግዚአብሔርን! በሕያው ነፍስህም እምላለሁ፥ አልለይህም አለ። ወደ ቤቴልም ወረዱ።"

2ኛ ነገሥት 2፥1-2

6. በቤቴል የነበረው ሁኔታ ሊለየው እስከማይችል ድረስ ኤልሳዕ ከኤልያስ ጋር ተጣብቆ ነበር።

"በቤቴልም የነበሩ የነቢያት ልጆች ወደ ኤልሳዕ ወጥተው እግዚአብሔር ጌታህን ከራስህ ላይ ዛሬ እንዲወስደው አውቀሃልን? አሉት። እርሱም፦ አዎን፥ አውቄአለሁ ዝም በሉ አላቸው።"

2ኛ ነገሥት 2፥3

7. በኢያሪኮ ያጋጠመው ነገርና ጫና ሊለየው እስከማይችል ድረስ ኤልሳዕ ከኤልያስ ጋር ተጣብቆ ነበር።

"ኤልያስም፦ኤልሳዕ ሆይ፥ እግዚአብሔር ወደ ኢያሪኮ ልኮኛልና እባክህ፥ በዚህ ቆይ አለው። እርሱም፦ ሕያው እግዚአብሔርን! በሕያው ነፍስህም እምላለሁ፥ አልለይህም አለ።"

2ኛ ነገሥት 2፥4

8. በዮርዳኖስ ባህር ያጋጠመው ችግር ሊለየው እስከማይችል ድረስ ኤልሳዕ ከኤልያስ ጋር ተጣብቆ ነበር።

"ኤልያስም እግዚአብሔር ወደ ዮርዳኖስ ልኮኛልና እባክህ፥ በዚህ ቆይ አለው። እርሱም፦ ሕያው እግዚአብሔርን! በሕያው ነፍስህም እምላለሁ፥ አልለይህም አለ። ሁለቱም ሄዱ።"

2ኛ ነገሥት 2፥6

9. ኤልሳዕ ከኤልያስ ጋር ተጣብቆ ስለነበር እስከመጨረሻይቱ ሰዓት ድረስ አይኖቹ በኤልያስ ላይ ተተክለው ነበር። ኤልሳዕ ቅባት የመቀበሉ ምስጢር አይኑን እስከመጨረሻ ድረስ በኤልያስ ላይ ማድረጉ እንደሆነ ተነግሮታል።

"ከተሻገሩም በኋላ ኤልያስ ኤልሳዕን፦ ከአንተ ሳልወሰድ አደርግልህ ዘንድ የምትሻውን ለምን አለው። ኤልሳዕም መንፈስህ በእኔ ላይ ሁለት እጥፍ ይሆን ዘንድ እለምንሃለሁ

አለ። እርሱም፦ አስቸጋሪ ነገር ለምነሃል፤ ነገር ግን ከአንተ ዘንድ በተወሰድሁ ጊዜ ብታየኝ ይሆንልሃል፤ አለዚያ ግን አይሆንልህም አለ።"

2ኛ ነገሥት 2፡9-10

10. ኤልሳዕን ከአባቱ ከኤልያስ ሊለይ የሚችለው መለኮታዊ ነገር ብቻ ነበር። ብዙ አገልጋዮች ከመንፈሳዊ አባቶቻቸው የሚለያዩት በሥጋዊነት፣ በጭቅጭቅና በቅናት ምክንያት ነው። በግጭት ምክንያት እጅግ ከሚያስፈልጓቸው ሰዎች ይለያሉ። እግዚአብሔር ካገናኘህ አካል ሊለይህ የሚችለው መለኮታዊ ጣልቃ ገብነት ብቻ እንደሆነ ወደሚያውቅ መንፈሳዊ መረዳት ውስጥ መግባት አለብህ። መለኮታዊ ጣልቃ ገብነት ብቻ ሊለይ ወደሚችል እግዚአብሔር ወደአገናኘህ አካል መመለስ አለብህ።

"ሲሄዱም እያዘገሙም ሲጫወቱ፥ እነሆ፥ የእሳት ሰረገላና የእሳት ፈረሶች በመካከላቸው ገብተው ከፈሉአቸው፤ ኤልያስም በዐውሎ ነፋስ ወደ ሰማይ ወጣ።"

2ኛ ነገሥት 2፡11

## ምዕራፍ 53

# የአገልግሎት እንቅፋቶች

**"እርሱ ግን ዘወር ብሎ ጴጥሮስን ወደኋላዬ ሂድ፥ አንተ ሰይጣን፤ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና ዕንቅፋት ሆነህብኛል አለው።"**

**ማቴዎስ 16፡23**

በዚህ ምንባብ ውስጥ ኢየሱስ ለአገልግሎቱ እንቅፋት ሊሆንበት የሚችለውን ነገር በግልጽ አስቀምጧል። ላይ ላዩን ስታዩት ዕንቅፋቱ ሰይጣን ነው ብለህ ታስብ ይሆናል። ነገር ግን ዕንቅፋቱ ከዚያ የረቀቀ ነበር። ለኢየሱስ አገልግሎት እንቅፋት የነበረው የሰዎች ግላዊ ፍላጎት ነበር።

እንቅፋት ማለት አንድን ነገር ከማከናወን የሚከለክልህ ችግር ነው። ስለሆነም እንቅፋት ጥሪህን የሚቋቋም መሰናክል፣አስቸጋሪ ነገር፣ የሚገድብ ነገር፣ወይም አጋጅ ነገር ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ እንቅፋቶቹ የሰዎች ፍላጎቶች እንደሆኑ ገልጧል! አንድ ሰው ስለአንድ ነገር የተለየ ፍላጎት ሲኖረው ከዚያ ነገር ጥቅም እንደሚያገኝ ስለሚያውቅ በዚያ ነገር ላይ ትኩረት ያደርጋል። የሰዎች ፍላጎት ለሰዎች ብዙ ጥቅም ሊሰጥ ይችል ይሆናል። ችግሩ ግን የሰዎች ፍላጎት ከእግዚአብሔር ፍለጎት የተለየ መሆኑ ነው።

የሰዎች ፍላጎቶች ከእግዚአብሔር ፍለጎቶች መለየታቸው ብቻ ሳይሆን የአገልግሎት እንቅፋቶች ናቸው። ስለሆነም ከጥሪህ ጋር የሚጻረሩ ናቸው።

ለዚህ ነው ሰዎች ያን ፍላጎታቸውን ለማሟላት ሲደክሙ አገልግሎታቸውን የሚያበላሹት። በአገልግሎቴ ዘመን የሰዎችን ፍላጎት ሲያገለግሉ ቆይተው መጨረሻቸው ረብ የሌለው የአገልግሎት ቁልል የሆነባቸውን ሰዎች ተመልክቻለሁ።

የሰዎችን ፍላጎት በማታገለግልበት ጊዜ ለራስህ የማታስብ ተደርገህ ልትታሰብ ትችላለህ። ለዚህ ምክንያቱ የሰዎችን ፍለጎት ብታገለግል በእርግጠኝነት የምድር ኑሮህ ስለሚሻሻል ነው። የሰዎች ፍላጎት ሰይጣናዊ ወይም የባዕድ አምልኮ እንቅስቃሴ አለመሆኑን ማሳሰብ

እፈልጋለሁ። የእነዚህ እንቅፋቶች ሚስጢሩ ለአንድ ሰው የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ፍላጎቶች መሆናቸው ነው። የሰዎች ፍላጎት ምግብ፣ ልብስ፣ ትዳር፣ ልጆች፣ ገንዘብ፣ ቤት፣ መኪና፣ ደህንነት፣ እና መረጋጋት የመሳሰሉትን ያካትታል።

## ለጥሪህ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ አሥራ ሁለት የሰው ፍላጎቶች

1. ምግብና ልብስ ክፉ ነገሮች አይደሉም። ነገር ግን ለልብስና ለምግብ የምትሮጥ ከሆነ ያ ለጥሪህ እንቅፋት ሊሆንብህ ይችላል።
2. ትዳር ክፉ አይደለም፣ ነገር ግን ለትዳር ከምንም በላይ የምትሮጥ ከሆነ ትዳር ለጥሪህ እንቅፋት ሊሆንብህ ይችላል።
3. ልጆችን መውለድና ማሳደግ ክፋት የለበትም ነገር ግን እንደዋና ነገር የምትሮጥለት ከሆነ ለጥሪህ እንቅፋት ሊሆን ይችላል።
4. ገንዘብ ክፉ ነገር አይደለም ነገር ግን እንደዋና ነገር የምትሮጥለት ከሆነ ለጥሪህ እንቅፋት ሊሆን ይችላል።
5. ቤት ቢኖርህ ክፉ ነገር አይደለም፣ ነገር ግን እንደዋና ነገር የምትሮጥለት ከሆነ ለጥሪህ እንቅፋት ሊሆን ይችላል።
6. መኪና ክፉ ነገር አይደለም ነገር ግን እንደዋና ነገር የምትሮጥለት ከሆነ ለጥሪህ እንቅፋት ሊሆን ይችላል።
7. በአንድ የተለየ ቦታ መኖር ክፉ ነገር አይደለም ነገር ግን በዚያ የተለየ ሥፍራ ለመኖር የምትሄደው ምህረት የለሽ አካሄድ ለጥሪህ እንቅፋት ነው።
8. ተፈላጊ ሰው መሆን ክፉ ነገር አይደለም ነገር ግን ተፈላጊ ለመሆን የምታደርገው ሩጫ ለጥሪህ እንቅፋት ነው።
9. ደህንነት (የጥበቃ አገልግሎት ማግኘት) ክፉ ነገር አይደለም ነገር ግን ደህንነትና ጥበቃ ለማግኘት የምትሮጠው ሩጫ ለጥሪህ እንቅፋት ሊሆን ይችላል።

10. የተሻለ ምድራዊ ኑሮ ክፋት የለበትም ነገር ግን ወደ ከፍተኛ የኑሮ ደረጃ ለመድረስ ያለህ ምኞት ለጥሪህ እንቅፋት ሊሆንብህ ይችላል፡፡

11. መደላደል ክፋት የለበትም ነገር ግን የተደላደለ ህይወት ለማመቻቸት የምታደርገው እረፍት የለሽ ሩጫ ለጥሪህ እንቅፋት ሊሆን ይችላል፡፡

12. ትምህርት መልካም ነገር ነው ነገር ግን እንደዋና ነገር የምትሮጥለት ከሆነ ለጥሪህ እንቅፋት ሊሆን ይችላል፡፡

## ምዕራፍ 54

# በክፉ ቀን የሚከሰትን መዘግየት ማሸነፍ

*"የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ። መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ። ስለዚህ በክፉው ቀን ለመቃወም፥ ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሡ።"*

ኤፌሶን 6፡11-13

አንድን ቀን ክፉ የሚያሰኘው ምንድነው? የዘገዩ ነገሮች አንድን ቀን ወደ ክፉ ይቀይራል! መልካምን ቀን ወደ ክፉ ቀን የሚቀይሩ ብዙ ነገሮች አሉ። ፈተናና መከራ ‹‹ክፉ ቀን›› ወደሚባል ሁኔታ ውስጥ ሊያስገባህ ይችላል። የዘገዩ ነገሮች ፈተናና መከራን ሊያስከትሉ ይችላሉ።

ነገሮች በዘገዩ ጊዜ፣ ነገሮች እንዴት እንደሚለወጡ የሚያሳዩ ብዙ ክፍሎች በመፅሐፍ ቅዱስ ይገኛሉ። በርካታ መልካም ሰዎች፣ ነገሮች በዘገዩባቸው ጊዜ ወደ ክፉነት ይለወጣሉ። ጌታው በዘገየ ጊዜ ያ ክፉ ባሪያ ወደ ሰካራምነት እንደተለወጠ አስታውስ። ‹‹ ያ ክፉ ባሪያ ግን ጌታዬ እስኪመጣ ይዘገያል ብሎ በልቡ ቢያስብ፥ ባልንጀሮቹን ባሮች ሊመታ ቢጀምር ከሰካሮችም ጋር ቢበላና ቢጠጣ፥...›› (ማቴዎስ 24፡ 48-49)

ከዚህ በተጨማሪ በመዘግየት ጊዜ የሰው ድካም ሲገለጥ ትመለከተላህ። ‹‹ሙሽራውም በዘገየ ጊዜ ሁሉ እንቅልፍ እንቅልፍ አላቸውና ተኙ።››(ማቴዎስ 25፡5)

የሰው ድካም፣ ፈተና እና አጋንንታዊ እንቅስቃሴዎች ተዳምረው በህይወትህ ክፉ ቀንን ይፈጥራሉ። ላንተ ግን ክፉ ቀን ወደ ድል ቀን ሊለወጥ ይችላል። በመረዳትህ ልክ የእግዚአብሔር ክንድ ሲሰራ ታያለህ። ወደ መልካም ፍጻሜ ያደርስሀል።

በአገልግሎት ውስጥ የሚከሰቱ መዘግየቶችን ለማሸነፍ ሶስት ነገሮችን ማድረግ ያስፈልጋል።

1. በእርግጠኝነት መዘግየትን በህይወትህና በአገልግሎትህ እንደሚከሰት ጠብቅ።
2. መዘግየት ለምንና እንዴት እንደሚከሰቱ አስተውል። ኢየሱስ ደግሞ ደጋግሞ የእግዚአብሔር ተስፋ እጅግ በዘገየ ጊዜ ሰዎች እንዴት ከመንገድ እንደሚስቱ ይነግራቸው ነበር።
3. መዘግየትን ምናልባት ሊከሰት ለሚችል ተጨማሪ መዘግየት ጭምር በመዘጋጀት ጠብቀው። አሥሩ ቆነጃጅት ያደረጉትን አድርግ። ተጨማሪ ዘይት በመያዝ በህይወትህና በአገልግሎትህ ሊከሰት ለሚችል ተጨማሪ መዘግየት ተዘጋጅ።

"ልባሞቹ ግን ከመብራታቸው ጋር በማሰሮአቸው ዘይት ያዙ።"

ማቴዎስ 25፡4

## ልትጠባበቃቸው የሚገቡህ ሃያ መዘግየቶች

1. የጌታን መምጫ መዘግየት መጠበቅ አለብህ።

"እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ታገሡ። እነሆ፥ ገበሬው የፊተኛውንና የኋለኛውን ዝናብ እስኪቀበል ድረስ እርሱን እየታገሠ የከበረውን የመሬት ፍሬ ይጠብቃል።"

ያዕቆብ 5፡7

2. እግዚአብሔር ከሰጠህ ተስፋዎች አንዳንዶቹ ሊዘገዩ እንደሚችሉ መጠበቅ አለብህ።

"ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፥ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል።

2ኛ ጴጥሮስ 3፡9

3. ትዳር በመመስረት ሂደት ውስጥ መዘግየት ሊከሰት እንደሚችል መጠበቅ አለብህ።

"ያዕቆብም ራሔልን ወደደ፤ እንዲህም አለ፦ ስለ ታናሺቱ ልጅህ ስለራሔል ሰባት ዓመት እገዛልሃለሁ። ላባም ለሌላ ሰው ከምሰጣት ይልቅ ለአንተ ብሰጣት ይሻላል ከእኔ ጋር ተቀመጥ አለ። ያዕቆብም ስለ ራሔል ሰባት ዓመት ተገዛ። እርስዋንም ይወድዳት ስለነበረ በእርሱ ዘንድ እንደ ጥቂት ቀን ሆነለት።"

ዘፍጥረት 29፡18-20

"ይህችንም ሳምንት ፈጽም፤ ሌላ ሰባት ዓመት ደግሞ እኔን ስለምታገለግለኝ አገልግሎት እርስዋን ደግሞ እሰጥሃለሁ። ያዕቆብም እንዲህ አደረገ፥ ይህችንም ሳምንት ፈጸመ፤ ልጁን ራሔልንም ለእርሱ ሚስት ትሆን ዘንድ ሰጠው።"

ዘፍጥረት 29፡27-28

## 4. ልጅ በመውለድ መዘግየት ሊከሰት እንደሚችል መጠበቅ አለብህ።

"ሕልቃና የሚሠዋበት ቀን በደረሰ ጊዜም ለሚስቱ ለፍናና ለወንዶችና ለሴቶች ልጆችዋ ሁሉ እድል ፈንታቸውን ሰጣቸው። ሐናንም ይወድድ ነበርና ለሐና ሁለት እጥፍ እድል ፈንታ ሰጣት። እግዚአብሔር ግን ማኅፀንዋን ዘግቶ ነበር። እግዚአብሔርም ማኅፀንዋን ዘግቶ ነበርና ጣውንትዋ ታስቆጣት ታበሳጫትም ነበር። በየዓመቱም እንዲህ ባደረገ ጊዜ እርስዋም ወደ እግዚአብሔር በምትወጣበት ጊዜ ታበሳጫት ነበር፤ ሐናም ታለቅስ ነበር፥ እንዳችም አትቀምስም ነበር።"

1ኛ ሳሙኤል 1፡4-7

"እነሆም ዘመድሽ ኤልሳቤጥ፥ እርስዋ ደግሞ በእርጅናዋ ወንድ ልጅ ፀንሳለች፥ ለእርስዋም መካን ትባል ለነበረችው ይህ ስድስተኛ ወር ነው፤ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና።"

ሉቃስ 1፡36-37

## 5. ዕድገትህ ሊዘገይ እንደሚችል መጠበቅ አለብህ።

አቤቱ፥ እስከ መቼ ፈጽመህ ትረሳኛለህ? እስከ መቼስ ፊትህን ከእኔ ትሰውራለህ? እስከ መቼ በነፍሴ እመካከራለሁ? ትካዜስ እስከ መቼ ሁልጊዜ ይሆናል? እስከ መቼ ጠላቴ በላዬ ይጓደዳል?

መዝሙር 13፡1-2

## 6. የእግዚአብሔር ቅባትና ስጦታ ሊዘገይብህ እንደሚችል መጠበቅ አለብህ።

"ምልክታችንን አናይም፤ ከእንግዲህ ወዲህም ነቢይ የለም፤ እስከ መቼ እንዲኖር የሚያውቅ በኛ ዘንድ የለም። አቤቱ፥ ጠላት እስከ መቼ ይሳደባል? ስምህን ጠላት ሁልጊዜ ያቃልላልን?"

መዝሙር 74፡9-10

## 7. ሰዎች ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ሊዘገዩ እንደሚችሉ መጠበቅ አለብህ።

"ኤልያስም ወደ ሕዝቡ ሁሉ ቀርቦ እስከ መቼ ድረስ በሁለት አሳብ ታነክሳላችሁ? እግዚአብሔር አምላክ ቢሆን እርሱን ተከተሉ፤ በአል ግን አምላክ ቢሆን እርሱን ተከተሉ አለ። ሕዝቡም አንዲት ቃል አልመለሱለትም።

1ኛ ነገሥት 18፡21

## 8. እግዚአብሔር አገልግሎትህን እስኪያሰፋው ሊዘገይ እንደሚችል መጠበቅ አለብህ፡፡

"አቤቱ፥ መልሰን፥ ፊትህንም አብራ፥ እኛም እንድናለን።
የሠራዊት አምላክ አቤቱ፥ በባሪያህ ጸሎት ላይ እስከ መቼ ትቈጣለህ?
የእንባ እንጀራን ትመግበናለህ፥ እንባም በስፍር ታጠጣናለህ።
ለጎረቤቶቻችን ክርክር አደረግኸን፥ ጠላቶቻችንም በላያችን ተሣለቁብን።
የሠራዊት አምላክ አቤቱ፥ መልሰን፥ ፊትህንም አብራ፥ እኛም እንድናለን።"

መዝሙር 80፡3-7

## 9. ባለጸጋ ለመሆን ጊዜ እንደሚወስድ መጠበቅ አለብህ፡፡

"አቤቱ፥ ከአንተ ጋር በተምዋገትሁ ጊዜ አንተ ጻድቅ ነህ፤ ነገር ግን ከአንተ ጋር ስለ ፍርድ ልናገር። የኃጢአተኞች መንገድ ስለምን ይቀናል? በደልን ስለሚያደርጉ ሁሉ ስለምን ደኅንነት ይሆናል? ተከለሃቸዋል፤ ሥር ሰድደዋል፤ አድገዋል፤ አፍርተውማል፤ በአፋቸው አንተ ቅርብ ነህ፥ ከልባቸው ግን ሩቅ ነህ። አንተ ግን፥ አቤቱ፥ አውቀኸኛል፤ አይተኸኛል፥ ልቤንም በፊትህ ፈትነሃል፤ እንደ በጎች ለመታረድ ጐትተህ ለያቸው፥ ለመታረድም ቀን አዘጋጃቸው። ምድሪቱ የምታለቅሰው፥ የአገሩ ሣርስ ሁሉ የሚደርቀው እስከ መቼ ነው? የተቀመጡባት ሰዎች ፍጻሜያችንን አያይም ብለዋልና ስለክፋታቸው እንስሶችና ወፎች ጠፍተዋል።"

ኤርምያስ 12፡1-4

## 10. ህልምህ እስኪከናወን ሊዘገይ እንደሚችል መጠበቅ አለብህ፡፡

"ከእስራኤልም ልጆች ርስት ያልተካፈሉ ሰባት ነገድ ቀርተው ነበር። ኢያሱም የእስራኤልን ልጆች አላቸው። የአባቶቻችሁ አምላክ እግዚአብሔር የሰጣችሁን ምድር ትወርሱ ዘንድ እስከ መቼ ለመግባት ቸል ትላላችሁ?"

ኢያሱ 18፡2-3

## 11. የቤተክርስቲያን አባሎችህ ያስተማርካቸውን ለማስተዋል ጊዜ እንደሚወስድ መጠበቅ አለብህ፡፡

"ሙሴም፡- የእግዚአብሔር ሰንበት ዛሬ ነውና ብሉት ዛሬ በሜዳ አታገኙትም። ስድስት ቀን ልቀሙት፤ ሰባተኛው ቀን ግን ሰንበት ነው፤ በእርሱ አይገኝም አለ።

በሰባተኛውም ቀን እንዲህ ሆነ፤ ከሕዝቡ አንዳንድ ሰዎች ሊለቅሙ ወጡ፥ ምንምን አላገኙም። እግዚአብሔርም ሙሴን ትእዛዞቼንና ሕጎቼን ለመጠበቅ እስከ መቼ እንቢ ትላላችሁ?"

ዘጸአት 16፡ 25-28

## 12. በተቃዋሚዎች ላይ ድል የምታገኝበት ጊዜ ሊዘገይ እንደሚችል መጠበቅ አለብህ።

"ሙሴም አሮንም ወደፈርዖን ገቡ፥ አሉትም። የዕብራውያን አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- በፊቴ ለመዋረድ እስከ መቼ እንቢ ትላለህ? ያገለግሉኝ ዘንድ ሕዝቤን ልቀቅ።"

ዘጸአት 10፡3

## 13. ሰዎች ጥሪህን ለመቀበል ሊዘገዩ እንደሚችሉ መጠበቅ አለብህ።

"እግዚአብሔርም ሙሴን ይህ ሕዝብ እስከ መቼ ይንቀኛል? በፊቱስ ባደረግሁት ተአምራት ሁሉ እስከ መቼ አያምኑብኝም?"

ዘኁልቁ 14፡11

## 14. አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ማሸነፍ ጊዜ ሊወስድ እንደሚችል መጠበቅ አለብህ።

"ኢዮብም መለሰ እንዲህም አለ፡- ነፍሴን የምትነዘንዙ፥ በቃልስ የምታደቅቁኝ እስከ መቼ ነው? ይኸው ስትሰድቡኝ አሥር ጊዜ ነው ስታሳክሩኝም አላፈራችሁም። በእውነትም የሳትሁ እንደሆነ፥ ስሕተቴ ከእኔ ጋር ትኖራለች። በእውነትም ብትጓደዱብኝ፥ መዋረዴን በእኔ ላይ ብትከራከሩ፥ እንግዲህ እግዚአብሔር እንደገለበጠኝ፥ በመረቡም እንደከበበኝ እወቁ።"

ኢዮብ 19፡1-6

## 15. የቤተክርስቲያን አባሎችህ የህይወት አረማመድ ከማስተካከል ሊዘገዩ እንደሚችሉ መጠበቅ አለብህ።

እናንተ የሰው ልጆች፥ እስከ መቼ ድረስ ልባችሁን ታከብዳላችሁ? እግዚአብሔር በጻድቁ እንደ ተገለጠ እወቁ እግዚአብሔር ወደ እርሱ በተጣራሁ ጊዜ ይሰማኛል።

መዝሙር 4፡2-3

## 16. ፈውስና ታምራት ሊዘገይ እንደሚችል መጠበቅ አለብህ።

"ድውይ ነኝና አቤቱ፥ ማረኝ፤ አጥንቶቼ ታውከዋልና ፈውሰኝ። ነፍሴም እጅግ ታወከች፤ አንተም አቤቱ፥ እስከ መቼ ድረስ ነው?"

መዝሙር 6፡2-3

## 17. ክፉዎች ወደ ፍርድ እስኪመጡ ሊዘገይ እንደሚችል መጠበቅ አለብህ።

"አቤቱ፥ ኃጢአተኞች እስከመቼ ይጓደዳሉ?
ይከራከራሉ፥ ዓመፃንም ይናገራሉ፤ ዓመፃንም የሚያደርጉ ሁሉ ይናገራሉ።
አቤቱ፥ ሕዝብን አዋረዱ፥ ርስትህንም አስቸገሩ።
ባልቴቲቱንና ድሀ አደጉን ገደሉ፥ ስደተኛውንም ገደሉ።
እግዚአብሔር አያይም፥ የያዕቆብ አምላክ አያስተውልም አሉ።"

መዝሙር 94፡3-7

## 18. ሞኞች ጠቢባን ከመሆን ሊዘገዩ እንደሚችሉ መጠበቅ አለብህ።

"ጥበብ በጎዳና ትጮኻለች፤ በአደባባይ ድምፅዋን ከፍ ታደርጋለች፤ በአደባባይ ትጣራለች። በከተማይቱ መግቢያ በር ቃሏን ትናገራለች። እናንተ አላዋቂዎች፥ እስከ መቼ አላዋቂነት ትወድዳላችሁ? ፌዘኞችም ፌዝን ይፈቅዳሉ? ሰነፎችም እውቀትን ይጠላሉ? ወደ ዘለፋዬ ተመለሱ እነሆ፥ መንፈሴን አፈስስላችኋለሁ፤ ቃሌን አስተምራችኋለሁ።"

ምሳሌ 1፡20-23

## 19. ሰነፎች ጠንካራ ሠራተኞች እስኪሆኑ ድረስ ሊዘገዩ እንደሚችሉ መጠበቅ አለብህ።

"አንተ ታካች፥ እስከ መቼ ትተኛለህ? ከእንቅልፍህስ መቼ ትነሣለህ? ጥቂት ትተኛለህ፥ ጥቂት ታንቀላፋለህ፥ ትተኛም ዘንድ ጥቂት እጅህን ታጥፋለህ እንግዲህ ድህነትህ እንደ ወንበዴ፥ ችጋርህም ሰይፍ እንደ ታጠቀ ሰው ይመጣብሃል።"

ምሳሌ 6፡9-11

## 20. ሌቦች ፍርድን እስኪያገኙ ሊዘገይ እንደሚችል መጠበቅ አለብህ።

ብዙ ሌቦች ገና እንዳልተያዙ ተመልክተህ ይሆናል። ከሰረቁት ነገር ጋር የተሰወሩ ይመስላሉ። ነገር ግን ‹‹ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና፤›› (ገላትያ 6፡7) የሚለው የእግዚአብሔር ቃል ሊሻር አይችልም።

"እንዚህ ሁሉ እርሱ ያልሆነውን ወደ እርሱ ለሚሰበስብ መያዣውንም ለራሱ የሚያበዛ ወዮለት! እስከ መቼ ነው? እያሉ ምሳሌ አይመስሉበትምን?"

ዕንባቆም 2፡6

## ምዕራፍ 55

# መዘግየት በሚከሰትበት ጊዜ የሚነሱ አሥራ አምስት ክፉ ነገሮች

1. መዘግየት በሚከሰትበት ጊዜ ብዙ ሰዎች መጥፎ ነገር ማሰብ ይጀምራሉ፡፡ የእግዚአብሔር በረከት እንደዘገየበት በሚያስብ ሰው አዕምሮ ውስጥ ክፉ ሀሳብ ያለ ችግር ይስተናገዳል፡፡

ጌታው መጥቶ እንዲህ ሲያደርግ የሚያገኘው ያ ባሪያ ብፁዕ ነው፤

እውነት እላችኋለሁ፥ ባለው ሁሉ ላይ ይሾመዋል።

ያ ክፉ ባሪያ ግን ጌታዬ እስኪመጣ ይዘገያል ብሎ በልቡ ቢያስብ፥

ባልንጀሮቹን ባሮች ሊመታ ቢጀምር ከሰካሮችም ጋር ቢበላና ቢጠጣ፥ የዚያ ባሪያ ጌታ ባልጠበቃት ቀን ባላወቃትም ሰዓት ይመጣል፥ ከሁለትም ይሰነጥቀዋል፥ እድሉንም ከግብዞች ጋር ያደርግበታል፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።

ማቴዎስ 24፡46-51

2. መዘግየት በሚከሰትበት ጊዜ ብዙ ሰዎች መጥፎ አመለካከቶች ይኖራቸዋል፡፡ የእግዚአብሔር በረከት እንደዘገየበት በሚያስቡ ሰዎች አዕምሮ ውስጥ ክፉ አመለካከቶች ያለ ችግር ይስተናገዳሉ፡፡

"ሕዝቡም ሙሴ ከተራራው ሳይወርድ እንደዘገየ ባዩ ጊዜ፥ ወደ አሮን ተሰብስበ ይህ ከግብፅ ምድር ያወጣን ሰው ሙሴ ምን እንደሆነ አናውቅምና ተነሥተህ በፊታችን የሚሄዱ አማልክት ሥራልን አሉት።

ሕዝቡም ሁሉ በጆሮቻቸው ያሉትን የወርቅ ቀለበቶች ሰብረው ወደ አሮን አመጡለት።

ከእጃቸውም ተቀብሎ በመቅረጫ ቀረጸው፥ ቀልጦ የተሠራ ጥጃም አደረገው፤ እርሱም፦ እስራኤል ሆይ፥ እነዚህ ከግብፅ ምድር ያወጡህ አማልክትህ ናቸው አላቸው።

አሮንም ባየው ጊዜ መሠዊያን በፊቱ ሠራ፡፡ አሮንም ነገ የእግዚአብሔር በዓል ነው ሲል አወጀ።"

ዘጸአት 32፡1-5

3. **መዘግየት በሚከሰትበት ጊዜ እግዚአብሔር ብቻ ሊያደርገው የሚችለውን ነገር ለማከናወን የሥጋ ክንዳቸውን ይጠቀማሉ።**

"ሦራም አብራምን፦ እነሆ፥ እንዳልወልድ እግዚአብሔር ዘጋኝ ምናልባት ከእርስዋ በልጅ እታነጽ እንደሆነ ወደ እርስዋ ግባ አለችው።

አብራምም የሦራን ቃል ሰማ። አብራምም በከነዓን ምድር አሥር ዓመት ከተቀመጠ በኋላ፥ የአብራም ሚስት ሦራ ግብፃዊት ባሪያዋን አጋርን ወስዳ ለባልዋ ለአብራም ሚስት ትሆነው ዘንድ ሰጠችው።

እርሱም ወደ አጋር ገባ፥ አረገዘችም፤ እንዳረገዘችም ባየች ጊዜ እመቤትዋን በዓይንዋ አቃለለች።"

ዘፍጥረት 16፡2-4

4. **መዘግየት በሚከሰትበት ጊዜ ብዙዎች ዋና ጥሪያቸውን ይተዋሉ።**

"ጌታም አለ፦እንኪያስ ምግባቸውን በጊዜው ይሰጣቸው ዘንድ ጌታው በቤተሰዎቹ ላይ የሚሾመው ታማኝና ልባም መጋቢ ማን ነው?

ጌታው መጥቶ እንዲህ ሲያደርግ የሚያገኘው ያ ባሪያ ብፁዕ ነው።

እውነት እላችኋለሁ፥ ባለው ሁሉ ላይ ይሾመዋል።

ያ ባሪያ ግን ጌታዬ እስኪመጣ ይዘገያል ብሎ በልቡ ቢያስብ ሎሌዎችንና ገረዶችንም ይመታ፤ ይበላም፤ ይጠጣም፤ ይሰክርም ዘንድ ቢጀምር..."

ሉቃስ 12፡42-45

5. **መዘግየት በሚከሰትበት ጊዜ ሰዎች ለገጠማቸው ችግር ሁሉ መሪዎቻቸውን ማማረር ይጀምራሉ።**

ሙሴንም በግብፅ መቃብር ስላልኖረ በምድረበዳ እንሞት ዘንድ አወጣኸንን? ከግብፅ ታወጣን ዘንድ ይህ ያደረግህብን ምንድርነው?

በምድረበዳ ከምንሞት ብንገዛላቸው ይሻላልና ተወን፥ ለግብፃውያን እንገዛ ብለን በግብፅ ሳለን ያልንህ ቃል ይህ አይደለምን? አሉት።

ዘጸአት 14፡11-12

6. **መዘግየት በሚከሰትበት ጊዜ ሰዎች መራራ ይሆናሉ። እግዚአብሔርንና ቤተ ክርስቲያንን ይቀየማሉ። ቤተ ክርስቲያናቸውን ትተው ወደሌላ ይሄዳሉ። ሌሎች ደግሞ**

ሳልተመለሱ ጸሎቶቻቸው እርዳታ ፍለጋ ወደ ነቢያት አገልግሎት ይሄዳሉ።

"ባልዋም ሕልቃና ሐና ሆይ፥ ለምን ታለቅሻለሽ? ለምንስ አትቀምሺም? ለምንስ ልብሽ ያዝንብሻል? እኔስ ከአሥር ልጆች አልሻልልሽምን? አላት።

በሴሎ ከበሉና ከጠጡ በኋላ ሐና ተነሣች። ካህኑም ዔሊ በእግዚአብሔር መቅደስ መቃን አጠገብ በመንበሩ ላይ ተቀምጦ ነበር።

እርስዋም በልብዋ ትመረር ነበር፥ በእግዚአብሔር ፊት ጸለየች፥ ጽኑ ልቅሶም አለቀሰች።

እርስዋም፦ አቤቱ፥ የሠራዊት ጌታ ሆይ፥ የባሪያህን መዋረድ ተመልከተህ ብታስበኝ፥ እኔንም ባትረሳ፥ ለባሪያህም ወንድ ልጅ ብትሰጥ፥ ዕድሜውን ሁሉ ለእግዚአብሔር እሰጠዋለሁ፥ ምላጭም በራሱ ላይ አይደርስም ብላ ስእለት ተሳለች።"

1ኛ ሳሙኤል 1፡8-11

7. መዘግየት በሚከሰትበት ጊዜ ሰዎች ማመን የማይገባቸውን ነገር ማመን ይጀምራሉ።

"እነዚያ ቀኖችስ ባያጥሩ ሥጋ የለበሰ ሁሉ ባልዳነም ነበር፤ ነገር ግን እነዚያ ቀኖች ስለተመረጡት ሰዎች ያጥራሉ። በዚያን ጊዜ ማንም እነሆ፥ ክርስቶስ ከዚህ አለ ወይም ከዚያ አለ ቢላችሁ አትመኑ፤

ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፥ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ።"

ማቴዎስ 24፡22-24

8. መዘግየት በሚከሰትበት ጊዜ ሰዎች ሳይዘጋጁ ይያዛሉ።

"ሙሽራውም በዘገየ ጊዜ ሁሉ እንቅልፍ እንቅልፍ አላቸውና ተኙ።

እኩለ ሌሊትም ሲሆን እነሆ፥ ሙሽራው ይመጣል፥ ትቀበሉት ዘንድ ውጡ የሚል ውካታ ሆነ።

በዚያን ጊዜ እነዚያ ቆነጃጅት ሁሉ ተነሥና መብራታቸውን አዘጋጁ።

ሰነፎቹም ልባሞቹን መብራታችን ሊጠፋብን ነው፤ ከዘይታችሁ ስጡን አሉአቸው።"

ማቴዎስ 25፡5-8

9. መዘግየት በሚከሰትበት ጊዜ ብዙዎች ወደኋላ ያፈገፍጋሉ፤ ብርሀናቸውም ይጠፋል።

"በዚያን ጊዜ መንግሥተ ሰማያት መብራታቸውን ይዘው ሙሽራውን ሊቀበሉ የወጡ አሥር ቆነጃጅትን ትመስላለች። ከእነርሱም አምስቱ ሰነፎች፣ አምስቱም ልባሞች

ነበሩ። ሰነፎቹ መብራታቸውን ይዘው ከእነርሱ ጋር ዘይት አልያዙምና፤ ልባሞቹ ግን ከመብራታቸው ጋር በማሰሮአቸው ዘይት ያዙ። ሙሽራውም በዘገየ ጊዜ ሁሉ እንቅልፍ እንቅልፍ አላቸውና ተኙ። እኩለ ሌሊትም ሲሆን እነሆ፥ ሙሽራው ይመጣል፥ ትቀበሉት ዘንድ ውጡ የሚል ውካታ ሆነ። በዚያን ጊዜ እነዚያ ቆነጃጅት ሁሉ ተነሡና መብራታቸውን አዘጋጁ። ሰነፎቹም ልባሞቹን መብራታችን ሊጠፋብን ነው፤ ከዘይታችሁ ስጡን አሉአቸው። ልባሞቹ ግን መልሰው ምናልባት ለእኛና ለእናንተ ባይበቃስ፤ ይልቅስ ወደሚሸጡት ሄዳችሁ ለራሳችሁ ግዙ አሉአቸው።"

ማቴዎስ 25፡1-9

## 10. መዘግየት በሚከሰትበት ጊዜ ሰዎች ክፋትን ማድረግ ይጀምራሉ።

"ያ ክፉ ባሪያ ግን ጌታዬ እስኪመጣ ይዘገያል ብሎ በልቡ ቢያስብ፥ ባልንጀሮቹን ባሮች ሊመታ ቢጀምር ከሰካሮችም ጋር ቢበላና ቢጠጣ..."

ማቴዎስ 24፡48-49

## 11. መዘግየት በሚከሰትበት ጊዜ ብዙዎች ሥፍራቸውን ይስቃሉ።

"ሙሽራውም በዘገየ ጊዜ ሁሉ እንቅልፍ እንቅልፍ አላቸውና ተኙ። በኋላም ደግሞ የቀሩቱ ቆነጃጅት መጡና ጌታሆይ ጌታሆይ፥ ክፈትልን አሉ። እርሱ ግን መልሶ፦ እውነት እላችኋለሁ፥ አላውቃችሁም አለ።"

ማቴዎስ 25፡5፤ 11-12

## 12. መዘግየት በሚከሰትበት ጊዜ ብዙ ሰዎች ግብዞች ይሆናሉ።

"ያ ክፉ ባሪያ ግን ጌታዬ እስኪመጣ ይዘገያል ብሎ በልቡ ቢያስብ፥ ባልንጀሮቹን ባሮች ሊመታ ቢጀምር ከሰካሮችም ጋር ቢበላና ቢጠጣ፥ የዚያ ባሪያ ጌታ ባልጠበቃት ቀን ባላወቃትም ሰዓት ይመጣል፥ ከሁለትም ይሰነጥቀዋል፥ እድሉንም ከግብዞች ጋር ያደርግበታል፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።"

ማቴዎስ 24፡48-51

## 13. መዘግየት በሚከሰትበት ጊዜ አገልጋዮች እርስ በእርሳቸው መጋጨት ይጀምራሉ።

"ያ ክፉ ባሪያ ግን ጌታዬ እስኪመጣ ይዘገያል ብሎ በልቡ ቢያስብ፥ ባልንጀሮቹን ባሮች ሊመታ ቢጀምር ከሰካሮችም ጋር ቢበላና ቢጠጣ..."

ማቴዎስ 24፡48-49

## 14. መዘግየት በሚከሰትበት ጊዜ ብዙዎች ከጥሪያቸው ይስታሉ።

"ጌታው መጥቶ እንዲህ ሲያደርግ የሚያገኘው ያ ባሪያ ብፁዕ ነው። እውነት እላችኋለሁ፥ ባለው ሁሉ ላይ ይሾመዋል። ያ ባሪያ ግን ጌታዬ እስኪመጣ ይዘገያል ብሎ በልቡ ቢያስብ ሎሌዎችንና ገረዶችንም ይመታ፤ ይበላም፤ ይጠጣም፤ ይሰክርም ዘንድ ቢጀምር፥ የዚያ ባሪያ ጌታ ባልጠበቃት ቀን ባላወቃትም ሰዓት ይመጣል፥ ከሁለትም ይሰነጥቀዋል፥ እድሉንም ከግብዞች ጋር ያደርግበታል፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።"

ማቴዎስ 24፡46-51

## 15. መዘግየት በሚከሰትበት ጊዜ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ንቀው ልክ እግዚአብሔር እንደሌለ ቆጥረው ህይወታቸውን እንደፈለጉ ይመራሉ።

የኖኅ ዘመን እንደነበረ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናልና። በዚያች ወራት ከጥፋት ውኃ በፊት፥ ኖኅ ወደ መርከብ እስከገባበት ቀን ድረስ፥ ሲበሉና ሲጠጡ ሲያገቡና ሲጋቡም እንደነበሩ፥ የጥፋት ውኃም መጥቶ ሁሉን እስከወሰደ ድረስ እንዳላወቁ፥ የሰው ልጅ መምጣት ደግሞ እንዲሁ ይሆናል። በዚያን ጊዜ ሁለት ሰዎች በእርሻ ይሆናሉ፤ አንዱ ይወሰዳል፤ አንዱም ይቀራል፤ ሁለት ሴቶች በወፍጮ ይፈጩሉ፤ አንዲቱ ትወሰዳለች፤ አንዲቱም ትቀራለች።

ማቴዎስ 24፡37-41

## ምዕራፍ 56

# መዘግየት የሚከሰትባቸው ስምንት ምክንያቶች

1. *እግዚአብሔር ለሁሉም ነገር ጊዜን ወስኗል።* እኔና አንተን ለማስደሰት ብሎ ሉአላዊነቱንና መለኮታዊነቱን መስዋዕት አያደርግም። የወደደውን እሱን ነው የሚያደርገው። እናም የወደደውን በወደደው ጊዜ ያደርጋል።

"ለሁሉ ዘመን አለው፥ ከሰማይ በታችም ለሆነ ነገር ሁሉ ጊዜ አለው።"

መክብብ 3፡1

"በምድር ላይ የሰው ሕይወት ብርቱ ሰልፍ አይደለምን? ወራቱም እንደ ምንደኛ ወራት አይደለምን?"

ኢዮብ 7፡1

2. *እግዚአብሔር በአንዳንድ ፈተናዎች እንድናልፍ ይፈልጋል።* አንዳንድ ነገሮችን በማዘግየት ይፈትነናል። በልባችን ምን እንዳለ ይመረምረናል። ነገሮች ሲዘገዩ ምን አይነት ምላሽ እንድምንሰጥ ማየት ይፈልጋል። የሚዘገይብን ነገር በውስጣችን ያለውን ያወጣል።

"አምላክህ እግዚአብሔር ይፈትንህ ዘንድ፥ በልብህም ያለውን ትእዛዙን ትጠብቅ ወይም አትጠብቅ እንደሆነ ያውቅ ዘንድ፥ ሊያስጨንቅህ በእነዚህ በአርባ ዓመታት በምድረ በዳ የመራህን መንገድ ሁሉ አስብ።"

ዘዳግም 8፡2

3. *መዘግየት የሚከሰተው ራስህን ሊመጣ ላለው በረከት እንድታዘጋጅ ነው።* ለእግዚአብሔር በረከት ራስን ማዘጋጀት በጣም አስፈላጊ ነው። ከዚህ በታች በምንመለከተው ታሪክ ውስጥ ያለችው ሴት ዘይቱን ለመቀበል ዝግጅት ማድረግ ነበረባት።

"ከነቢያትም ወገን ሚስቶች አንዲት ሴት ባሌ ባሪያህ ሞቶአል ባሪያህም እግዚአብሔርን ይፈራ እንደነበረ አንተ ታውቃለህ ባለዕዳ ልጆቼን ባሪያዎች አድርጎ ሊወስዳቸው መጥቶአል ብላ ወደ ኤልሳዕ ጮኸች። ኤልሳዕም አደርግልሽ ዘንድ ምን ትሻለሽ? በቤትሽ ያለውን ንገሪኝ አላት። እርስዋም፡- ለእኔ ለባሪያህ ከዘይት ማሰሮ

በቀር በቤቴ አንዳች የለኝም አለች። እርሱም፦ ሄደሽ ከጐረቤቶችሽ ሁሉ ከሜዳ ባዶ ማድጋዎችን ተዋሺ አታሳንሻቸውም አላት።"

1ኛ ነገሥት 4፡1-3

4. *እምነትህን ለመፈተሽ መዘግየት ይከሰታል።* ሁለቱ ማየት የተሳናቸው ሰዎች ፈውሳቸውን ከመቀበላቸው በፊት ኢየሱስን ከገዢው ቤት እስከራሱ ቤት ድረስ ተከትለውት ነበር። እንዲፈውሳቸው ወደ ኢየሱስ ይጮሁ ነበር። እርሱ ግን ዝም አላቸው። ወደ ቤቱ ረጅም ርቀት ከተከተሉት በኋላ ዞር አለ። ‹‹ታምናላችሁን?›› ብሎ ጠየቃቸው። እንደ እውነቱ ከሆነ ገና ከኢያሪያስ ቤት እንደወጣ ሊፈውሳቸው ይችል ነበር። ነገር ግን ከመፈወሱ በፊት ሁለቱ ማየት የተሳናቸው ሰዎች በእርሱ የፈውስ ሐይል ማመናቸውን እርግጠኛ መሆን ፈልጎ ነበር።

"ኢየሱስም ከዚያ ሲያልፍ ሁለት ዕውሮች የዳዊት ልጅ ሆይ፥ ማረን ብለው እየጮሁ ተከተሉት። ወደ ቤትም በገባ ጊዜ ዕውሮቹ ወደ እርሱ ቀረቡ፥ ኢየሱስም፦ ይህን ማድረግ እንድችል ታምናላችሁን? አላቸው።አዎን፥ ጌታ ሆይ አሉት። በዚያን ጊዜ እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ ብሎ ዓይኖቻቸውን ዳሰሰ፤ ዓይኖቻቸውም ተከፈቱ።"

ማቴዎስ 9፡27-30

5. *ትዕግሥትን በአንተ ውስጥ ሊያፈራ መዘግየት ይከሰታል።* እምነትህ በተፈተነ ቁጥር በውስጥህ ትዕግሥትን ይፈጥራል። ምክንያቱም እምነት ሁልጊዜ ከትዕግሥት ጋር ነው የሚሰራው።

"የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ... "

ያዕቆብ 1፡3

6. *መዘግየት በመዋረድ ውስጥ የማለፍ ብቃትህን ለመፈተሽ ይከሰታል።* ከዚህ በታች በተመከተው የእግዚአብሔር ቃል ክፍል ውስጥ ‹‹ንዝነዛ›› የሚለው ቃል መሰረታዊ የግሪክ ቃል ትርጉሙ ‹‹አለማፈር›› የሚል ነው። እፍረትን ሳትጥል ከእግዚአብሔር ጋር ብዙ እርምጃ መጓዝ አትችልም። የነገሮች መዘግየት ብዙ ጊዜ ልታልፍባቸው የሚገባ አሳፋሪ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል። መኪና፣ ባል ወይም ልጅ የማግኛው ጊዜ ዘግይቶብህ ይሆናል። ያለ እነዚህ መታገልና በአካባቢህ ያሉ ሰዎች ስለአንተ የሚሰጡትን አስተያየትና የሚያሳዩትን አቋም መቋቋም ሊኖርብህ ይችላል።

"ያም ከውስጥ መልሶ፦ አታድክመኝ፤ አሁን ደጁ ተቈልፎአል፤ ልጆቼም ከእኔ ጋር በአልጋ ላይ አሉ፤ ተነሥቼ ልሰጥህ አልችልም ይላልን? እላችኋለሁ፥ ወዳጅ ስለሆነ ተነሥቶ ባይሰጠው እንኳ፥ ስለ ንዝነዛው ተነስቶ የሚፈልገውን ሁሉ ይሰጠዋል።"

ሉቃስ 11፡7-8

7. *ጽናትህን ለመፈተሽ መዘግየት ሊከሰት ይችላል፡፡ ጽናት በአንድ ነገር ላይ ያለህን እምነት መጠን የሚለካ የሚያሳይ ነው፡፡* በአንድ ነገር ታምን ይሆናል፡፡ ነገር ግን በጭፍን ማመን እምነትህን ፈተና ውስጥ ይከተዋል፡፡

"ያም ከውስጥ መልሶ፦ አታድክመኝ፤ አሁን ደጁ ተቈልፎአል፤ ልጆቼም ከእኔ ጋር በአልጋ ላይ አሉ፤ ተነሥቼ ልሰጥህ አልችልም ይላልን? እላችኋለሁ፥ ወዳጅ ስለሆነ ተነሥቶ ባይሰጠው እንኳ፥ ስለ ንዝነዛው ተነስቶ የሚፈልገውን ሁሉ ይሰጠዋል።"

ሉቃስ 11፡7-8

8. *ፍሬ የማፍራት እድል ታገኝ ዘንድ መዘግየት ሊከሰት ይችላል፡፡* ከዚህ ቀጥሎ በምናነበው ታሪክ ውስጥ የወይኑ እርሻ ባለቤት ዛፏ ፍሬ የማፍራት ሌላ እድል ለመስጠት በማሰብ የመቁረጥ ውሳኔውን በአንድ አመት ሲያራዝም እንመለከታለን፡፡ አንዳንድ ጊዜ በህይወትህ የሚከሰተው መዘግየት ወደ ሌላ አገልግሎት እንድትዘረጋ እግዚአብሔር እድል የሚሰጥበት መንገድ ይሆናል፡፡

"ይህንም ምሳሌ አለ። ለአንድ ሰው በወይኑ አትክልት የተተከለች በለስ ነበረችው፥ ፍሬም ሊፈልግባት መጥቶ ምንም አላገኘም። የወይን አትክልት ሠራተኛውንም፦ እነሆ፥ ከዚህች በለስ ፍሬ ልፈልግ ሦስት ዓመት እየመጣሁ ምንም አላገኘሁም፤ ቍረጣት፤ ስለምን ደግሞ መሬቱን ታጐሳቍላለች? አለው። እርሱ ግን መልሶ፦ ጌታ ሆይ፥ ዙሪያዋን እስክኰተኵትላትና ፋንድያ እስካፈስላት ድረስ በዚች ዓመት ደግሞ ተዋት። ወደ ፊትም ብታፈራ፥ ደኅና ነው፤ ያለዚያ ግን ትቈርጣታለህ አለው።"

ሉቃስ 13፡6-9

## ምዕራፍ 57

# የእግዚአብሔር እርዳታ የሌለበት አገልግሎት ምን ይመስላል?

"በሰማርያም ታላቅ ራብ ሆኖ ነበር፤ እነሆም፥ የአህያ ራስ በሰማኒያ ብር፥ የርግብም ኩስ የጎሞር ስምንተኛ የሚሆን በአምስት ብር እስኪሸጥ ድረስ ከበቡአት።

የእስራኤልም ንጉሥ በቅጥር ላይ በተመላለሰ ጊዜ አንዲት ሴት ጌታዬ ንጉሥ ሆይ፥ እርዳኝ ብላ ወደ እርሱ ጮኸች።

እርሱም፦ እግዚአብሔር ያልረዳሽን እኔ እንዴት እረዳሻለሁ? ከአውድማው ወይስ ከመጥመቂያው ነውን? አለ።"

2ኛ ነገሥት 6፡25-27

የንጉሡ ጩኸት ‹‹እግዚአብሔር ካልረዳችሁ እኔ እንዴት ልረዳችሁ እችላለሁ?›› የሚል ነው፡፡ ይህ የእያንዳንዱ መጋቢና እረኛ ጩኸት መሆን አለበት፡፡ እግዚአብሔር ካልረዳኝ ማንም ሊረዳኝ አይችልም! የሚለው እውነት የሁሉም መጋቢዎች የልብ እምነት መሆን አለበት፡፡

መጋቢው ይህን የሚያምን መሆኑ በተለያየ መንገድ ይገለጻል፡፡ እግዚአብሔር እንደሚረዳህ የምታምን ከሆነ ራስህን አብዝተህ ስትጸልይ ታገኘዋለህ፡፡ ቃሉን ስታጠና ራስህን ታገኘዋህ! እግዚአብሔርን በትዕግሥት ትጠብቀዋለህ፡፡ ይህን የምታደርገው ‹‹እግዚአብሔር ካልረዳኝ ማንም ሊረዳህ እንደማይችል›› ስለምታውቅ ነው፡፡

በአገልግሎት ውስጥ ያለ ሰው እርዳታው ከእግዚአብሔር እንደሚመጣ በትክክል ያውቃል ብለህ ታስብ ይሆናል፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ መጋቢዎች ናቸው እግዚአብሔርን የመጠበቅ ትዕግሥት የሌላቸው፡፡ ታላቁ የአገልግሎት ሚስጢር እግዚአብሔርን የመጠበቅ ሚስጢር ነው፡፡ እርዳታህ ሁሉ የሚመጣው ከእርሱ ነው፡፡ ለአንድ ቀን እግዚአብሔርን መጠበቅ ተለማመድ፡፡ አንድ ቀን ወስንና ለሰባት ተከታታይ ቀናት ለመጸሌ ሞክር፡፡ በአገልግሎትህ ልዩነትን የሚያመጣው የእግዚአብሔር እርዳታ እንደሆነ ይገለጥልሀል፡፡

በምድር ባለህ ህይወትና አገልግሎት ሁሉ እግዚአብሔርን መጠበቅ ቅድሚያ የምትሰጠውና የማታመቻምቸው ጉዳይ መሆን አለበት።

## ያለ እግዚአብሔር እርዳታ የሆነ ሕይወት ሰባት ምልክቶች

እግዚአብሔር በማይረዳህ ጊዜ ህይወትህ ምን እንደሚመስል እንድታውቅ እፈልጋለሁ። እግዚአብሔርን የማትጠብቅ ከሆነ አገልግሎትህ ምን መልክ እንደሚኖረው እንድትረዳ እፈልጋለሁ። ሀና እግዚአብሔር ያልረዳቸው ሰዎች እንዴት ለጥፋት እንደሆኑ ትናገራለች። ከራሷ ልምድ እግዚአብሔር ባይረዳት ኖሮ እንደማይከናወንላት ታውቅ ነበር። ያለ እግዚአብሔር እርዳታ መሆን ምን እንደሚመስል በሚገባ ታውቅ ነበር። እግዚአብሔር ሲቃወምህ ምን ማለት እንደሆነ ታውቅ ነበር።

1. እግዚአብሔር ካልረዳቸው ኃያላን ሰዎች እንኳ ይጠፋሉ።

"ሐናም ስትጸልይ እንዲህ አለች። ልቤ በእግዚአብሔር ጸና፥ ቀንዴ በእግዚአብሔር ከፍ ከፍ አለ አፌ በጠላቶቼ ላይ ተከፈተ፤ በማዳንህ ደስ ብሎኛል።

እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ የለምና፥ እንደ አምላካችንም ጻድቅ የለምና ከአንተ በቀር ቅዱስ የለም።

አትታበዩ፥ በኵራትም አትናገሩ፤ እግዚአብሔር አዋቂ ነውና፥ እግዚአብሔርም ሥራውን የሚመዝን ነውና፥ ከአፋችሁ የኵራት ነገር አይውጣ።

የኃያላንን ቀስት ሰብሮአል፥ ደካሞችንም በኃይል ታጥቀዋል።"

1ኛ ሳሙኤል 2፡1-4

2. እግዚአብሔር የማይረዳህ ከሆነ ሰዎች ለአንተና ለአገልግሎትህ ያላቸው ግምት የወረደ ይሆናል። ለአገልግሎትህ ለዳቦ ከሚሆን ክፍያ ያለፈ ነገር አይሰጡህም።

"ጠግበው የነበሩ እንጀራ አጡ፤ ተርበው የነበሩ ከራብ ዐርፈዋል፤ መካኒቱ ሰባት ወልዳለችና፥ ብዙም የወለደችው ደከማለች።"

1ኛ ሳሙኤል 2፡5

3. እግዚአብሔር የማይረዳህ ከሆነ ከመበርታት ይልቅ እየደከምህ ትመጣለህ።

"ጠግበው የነበሩ እንጀራ አጡ፤ ተርበው የነበሩ ከራብ ዐርፈዋል፤ መካኒቱ ሰባት ወልዳለችና፥ ብዙም የወለደችው ደከማለች።"

1ኛ ሳሙኤል 2፡5

4. እግዚአብሔር አገልግሎትህን ከተቃወመ ትሞታለህ።

"እግዚአብሔር ይገድላል፤ ያድናልም፤ ወደ ሲኦል ያወርዳል፥ ያወጣል።"

1ኛ ሳሙኤል 2፡6

5. እግዚአብሔር የማይረዳህ ከሆነ ድሀ ትሆናለህ።

"እግዚአብሔር ድሀ ያደርጋል፥ ባለጠጋም ያደርጋል፤ ያዋርዳል፥ ደግሞም ከፍ ከፍ ያደርጋል።"

1ኛ ሳሙኤል 2፡7

6. እግዚአብሔር የማይረዳህ ከሆነ ከደረጃህ ዝቅ ትላለህ።

"እግዚአብሔር ድሀ ያደርጋል፥ ባለጠጋም ያደርጋል፤ ያዋርዳል፥ ደግሞም ከፍ ከፍ ያደርጋል።"

1ኛ ሳሙኤል 2፡7

7. እግዚአብሔር የማይረዳህ ከሆነ የአገልግሎትህ ድምጽ አይሰማም።

"እርሱ የቅዱሳኑን እግር ይጠብቃል፤ ኃጥአን ግን ዝም ብለው በጨለማ ይቀመጣሉ፤ ሰው በኃይሉ አይበረታምና።"

1ኛ ሳሙኤል 2፡9

*ምዕራፍ 58*

# እግዚአብሔር ሲያሳድግህ ያለው ሁኔታ ምን ይመስላል?

እግዚአብሔር አገልጋዮቹን እንደሚያሰፋና እንደሚያሳድግ ተስፋ ሰጥቷል። እርሱ ከፍ ያደርግሃል፤ ያበለጽግሃማል። የምትዘራውን ያንኑ ታጭዳለህ። በጌታ ልብ ውስጥ የነበረው ሸክም በጎቹን የመንከባከብና ለበጎቹ የመጠንቀቅ ሸክም ነበር።

‹‹በጎቼን አሰማራ›› ልብ የሚነካ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የሰጠው የመጨረሻ ትእዘዝ ነው። በጌታ ልብ ውስጥ ታላቅ ሥፍራ ያለውን ይህን ትዕዛዝ መታዘዝ ሽልማት እንዳለው የሚያጠራጥር አይደለም።

እምነት ለአገልግሎት በጣም አስፈላጊ ነው። መጋቢ የእምነት ሰው መሆን አለበት። ለቤተክርስቲያን እድገት የሚሆኑ ብዙ የምትጠብቃቸው ነገሮች መኖር አለባቸው። እግዚአብሔር እንደሚንከብህና መንጋህን እንደሚያሳስገው ማመን አለብህ። በእጆችህ ሥራዎች ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር በረከት እንዲመጣ በመጠበቅ ወደ ላይ መመልከት አለብህ። ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም! እንደሚባረክህና እንደሚሸልምህ ስታምን እግዚአብሔርን የበለጠ ደስ ታሰኘዋለህ።

እግዚአብሔር ሊረዳህና ሊያሳድግህ ተስፋ ሰጥቷል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሙሉ እግዚአብሔር አገልጋዮቹን በአንድም በሌላ መንገድ እንደሚረዳ ተስፋ ሰጥቷል። አገልግሎቴ ይወድቃል ብለህ አትፍራ። ጥሪህን እንድትፈጽም ከፍ ያደርግሃል፤ ያበረታሃልም። በጣም ብዙ መከራ. ችግርና ሌሎች ጉዳዮች ገጥመውህ ይሆናል በመጨረሻ ግን ሁሉንም ታሸንፋቸዋለህ።

ከእግዚአብሔር ቃል አጥብቀህ ልትይዛቸው የሚገባቸውን በርካታ የተለያዩ ተስፋዎች ላካፍለህ እፈልጋለሁ። እነኚህ የተስፋ ቃሎች ስለወደፊትህ የሚናገሩ ናቸው። ቀስ በቀስ የሚገለጠውን የህይወትህንና የአገልግትህን ፍሬ የሚተነብዩ ተስፋዎች ናቸው።

# ሠላሳ ስምንት የእድገት ተስፋዎች

1. እግዚአብሔር ጠርምሰህ እንደምትወጣ ተስፋ ሰጥቶሀል።

"በቀኝና በግራ ትሰፋፊያለሽና፥ ዘርሽም አሕዛብን ይወርሳልና፥ የፈረሱትንም ከተሞች መኖሪያ ያደርጋልና።

ኢሳይያስ 54፡3

2. እግዚአብሔር እንደማታፍርና እንደማትምታታ ተስፋ ሰጥቶሀል፡ ፡ በአገልግሎትህ ያጋጠመህን የብቸኝነት ዘመን ተመልሰህ አታስበውም።

"አታፍሪምና አትፍሪ፤ አትዋረጂምና አትደንግጪ፤ የሕፃንነትሽንም እፍረት ትረሺዋለሽ፥ የመበለትነትሽንም ስድብ ከእንግዲህ ወዲህ አታስቢም።"

ኢሳይያስ 54፡4

3. እግዚአብሔር ከመንጋህ ጋር ሊቀላቅልህ ተስፋ ሰጥቶሀል።

"ጥቂት ጊዜ ተውሁሽ፥ በታላቅም ምሕረት እሰበስብሻለሁ።"

ኢሳይያስ 54፡7

4. እግዚአብሔር ምህረትና ቸርነቱን እንደምትቀበል ተስፋ ሰጥቶሀል።

"... በዘላለምም ቸርነት እምርሻለሁ፥ ይላል ታዳጊሽ እግዚአብሔር፡-"

ኢሳይያስ 54፡8

5. እግዚአብሔር ልጆችህ ከእግዚአብሔር የተማሩ እንደሚሆኑና ሠላማቸውም እንደሚበዛ ተስፋ ተሰጥቶሀል።

"ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ፥ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል።"

ኢሳይያስ 54፡13

6. እግዚአብሔር በጽድቅ እንደምትታነጽ ተስፋ ሰጥቶሀል።

"በጽድቅ ትታነጺያለሽ፤ ከግፍ ራቂ፥ አትፈሪምም፥ ድንጋጤም ወደ አንቺ አትቀርብም።"

ኢሳይያስ 54፡14

7. እግዚአብሔር እንደማትጨቆን ተስፋ ሰጥቶሀል።

"...ከግፍ ራቂ..."

ኢሳይያስ 54፡14

8. ከድንጋጤና ከፍርሀት ነጻ እንደምትሆን እግዚአብሔር ተስፋ ሰጥቶሀል።

"...አትፈሪምም፥ ድንጋጤም ወደ አንቺ አትቀርብም።"

ኢሳይያስ 54፡14

9. እግዚአብሔር በአንተ ላይ የሚሰራ መሳሪያ እንደማይሰራ ተስፋ ሰጥቶሀል።

"በአንቺ ላይ የተሠራ መሣሪያ ሁሉ አይከናወንም..."

ኢሳይያስ 54፡17

10. እግዚአብሔር በከሳሾች፣ በውሸታሞችና በሀሜተኞች ላይ እንደምትሰልጥን ተስፋ ሰጥቶሀል።

"...በፍርድም በሚነሣብሽ ምላስ ሁሉ ትፈርጂበታለሽ።"

ኢሳይያስ 54፡17

11. እግዚአብሔር ከመሰሎችህ በላይ ሊያደርግህ ተስፋ ሰጥቶሀል።

"...አምላክህ እግዚአብሔር ከምድር አሕዛብ ሁሉ ላይ ከፍ ከፍ ያደርግሃል።"

ዘዳግም 28፡1

12. እግዚአብሔር በሄድክበት ሁሉ ሊባረክህ ተስፋ ሰጥቶሀል።

"አንተ በከተማ ቡሩክ ትሆናለህ፥ በእርሻም ቡሩክ ትሆናለህ።"

ዘዳግም 28፡3

13. እግዚአብሔር ልጆችህንና ከብቶችህን እንደሚባርክ ተስፋ ሰጥቶሀል።

"የሆድህ ፍሬ፥ የምድርህም ፍሬ፥ የከብትህም ፍሬ፥ የላምህም ርቢ፥ የበግህም ርቢ ቡሩክ ይሆናል።"

ዘዳግም 28፡4

14. እግዚአብሔር ያለህን ሊባርክ ተስፋ ሰጥቶሀል።

"እንቅብህና ቡሃቃህ ቡሩክ ይሆናል።"

ዘዳግም 28፡5

15. እግዚአብሔር በእንቅስቃሴህ ሁሉ በረከትን እንደሚሰጥህ ተስፋ ሰጥቶሀል።

"አንተም በመግባትህ ቡሩክ ትሆናለህ፥ በመውጣትህም ቡሩክ ትሆናለህ።"

ዘዳግም 28፡6

16. እግዚአብሔር ጠላቶችህን እንደሚበትን ተስፋ ሰጥቶሀል።

"እግዚአብሔርም በላይህ የሚቆሙትን ጠላቶችህን በፊትህ የተመቱ ያደርጋቸዋል፤ በአንድ መንገድ ይመጡብሃል፥ በሰባትም መንገድ ከፊትህ ይሸሻሉ።"

ዘዳግም 28:7

17. እግዚአብሔር የእጆችህን ሥራ እንደሚባርክ ተስፋ ሰጥቶሀል።

"እግዚአብሔር በረከቱ በአንተ ላይ በጎተራህ በእጅህም ሥራ ሁሉ እንዲወርድ ያዝዛል፤ አምላክህ እግዚአብሔር በሚሰጥህም ምድር ይባርክሃል።"

ዘዳግም 28:8

18. እግዚአብሔር ለራሱ ሊለይህ ተስፋ ሰጥቶሀል።

"የአምላክህን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ብትጠብቅ፥ በመንገዱም ብትሄድ፥ እግዚአብሔር እንደማለልህ ለእርሱ የተቀደሰ ሕዝብ አድርጎ ያቆምሃል።"

ዘዳግም 28:9

19. እግዚአብሔር በረከትህ ለሁሉ እንዲታይ እንደሚያደርግ ተስፋ ሰጥቶሀል።

"የምድር አሕዛብም ሁሉ የእግዚአብሔር ስም በአንተ ላይ እንደተጠራ አይተው ይፈሩሃል።"

ዘዳግም 28:10

20. እግዚአብሔር ፍሬያማ ሊያደርግህ ተስፋ ሰጥቶሀል።

"እግዚአብሔርም እርሱዋን ይሰጥህ ዘንድ ለአባቶችህ በማለላቸው በምድርህ ላይ፥ በሆድህ ፍሬ፥ በከብትህ ፍሬ፥ በእርሻህም ፍሬ፥ እግዚአብሔር በጎነቱን በላይህ ያበዛል።"

ዘዳግም 28:11

21. እግዚአብሔር ለሌሎች ማበደር ትችል ዘንድ አትረፍርፎ ሊሰጥህ ተስፋ ሰጥቶሀል።

"እግዚአብሔርም ለምድርህ በወራቱ ዝናብ ይሰጥ ዘንድ፥ የእጅህንም ሥራ ሁሉ ይባርክ ዘንድ መልካሙን መዝገብ ሰማዩን ይከፍትልሃል፤ ለብዙ አሕዝብም ታበድራለህ፥ አንተ ግን ከማንም አትበደርም።"

ዘዳግም 28:12

22. እግዚአብሔር ልቀህ እንደምትገኝ ተስፋ ሰጥቶሀል።

"ዛሬም ያዘዝሁህን የአምላክህን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሰምተህ ብትጠብቃት ብታደርጋትም፥ ዛሬም ካዘዝሁህ ከእነዚህ ቃሎች ወደ ቀኝ ወደ ግራም ፈቀቅ ባትል፥

ታመልካቸውም ዘንድ ሌሎችን አማልክት ባትከተል፥ እግዚአብሔር ራስ ያደርግሃል እንጂ ጅራት አያደርግህም፤ ሁልጊዜም በላይ እንጂ በታች አትሆንም።"

ዘዳግም 28፡13-14

23. እግዚአብሔር ልብህ በጌታ ደስ እንደሚለው ተስፋ ሰጥቶሀል፡፡

"ልቤ በእግዚአብሔር ደስ ይለዋል፤. . ."

1ኛ ሳሙኤል 2፡1 (አዲሱ ትርጉም 1980)

24. እግዚአብሔር ባለሥልጣን ሲያደርግህ ተስፋ ሰጥቶሀል፡፡

"ቀንዶ በእግዚአብሔር ከፍ ከፍ አለ..."

1ኛ ሳሙኤል 2፡1

25. እግዚአብሔር አሸናፊ እንደምትሆንና ስላለፉ መከራዎችህና ጠላቶችህ በድፍረት እንደምታወራ ተስፋ ሰጥቶሀል፡፡

"... አፌ በጠላቶቼ ላይ ተከፈተ፡፡"

1ኛ ሳሙኤል 2፡1

26. እግዚአብሔር በእግዚአብሔር ማዳን ደስ እንደምትሰኝ ተስፋ ሰጥቶሀል፡፡

"...በማዳንህ ደስ ብሎኛል።"

1ኛ ሳሙኤል 2፡1

27. እግዚአብሔር መከላከያህ እንደሚሆንልህ ተስፋ ሰጥቶሀል፡፡

"... አምላካችንን የሚመስልም መጠጊያ ምሽግ የለም፡፡"

1ኛ ሳሙኤል 2፡2 (አዲሱ ትርጉም 1980)

28. እግዚአብሔር በተሰናከልህ ጊዜ እንኳ ኃይልን እንደምትቀበል ተስፋ ሰጥቶሀል፡፡

"የኃያላንን ቀስት ሰብሮአል፥ ደካሞችንም በኃይል ታጥቀዋል።"

1ኛ ሳሙኤል 2፡4

29. እግዚአብሔር ከእንግዲህ በረሀብ እንደማትሰቃይ ተስፋ ሰጥቶሀል፡፡

". . .ተርበው የነበሩ ከራብ ዐርፈዋል. . ."

1ኛ ሳሙኤል 2፡5

30. እግዚአብሔር መካንነትህን አስወግዶ ፍሬያማ እንደሚያደርግህ ተስፋ ሰጥቶሀል።

"...መካኒቱሰባትወልዳለችና..."

1ኛ ሳሙኤል 2:5

31. እግዚአብሔር በህይወት እንደሚጠበቅህ ተስፋ ሰጥቶሀል።

"እግዚአብሔር ይገድላል፤ ያድናልም..."

1ኛ ሳሙኤል 2:6

32. እግዚአብሔር ከፍ እንደሚያደርግህ ተስፋ ሰጥቶሀል።

"...ወደሲኦል ያወርዳል፥ ያወጣል።"

1ኛ ሳሙኤል 2:6

33. እግዚአብሔር እንደሚያበለጽግህ ተስፋ ሰጥቶሀል።

"እግዚአብሔር ድሀ ያደርጋል፥ ባለጠጋም ያደርጋል..."

1ኛ ሳሙኤል 2:7

34. እግዚአብሔር ወደ ከፍታ እንደሚያወጣህ ተስፋ ሰጥቶሀል።

"ያዋርዳል፥ደግሞም ከፍከፍ ያደርጋል።"

1ኛ ሳሙኤል 2:7

35. እግዚአብሔር ከአመድ ላይ እንደሚያነሳህ ተስፋ ሰጥቶሀል።

"ችግረኛውን ከመሬት ያስነሣል..."

1ኛ ሳሙኤል 2:8

36. እግዚአብሔር ከመኳንንት ጋር እንድትቀመጥ እንደሚያደርግህ ተስፋ ሰጥቶሀል።

"ከሕዝቡ መኳንንት ጋር ያስቀምጣቸው ዘንድ፥ የክብርንም ዙፋን ያወርሳቸው ዘንድ፥ ችግረኛውን ከመሬት ያስነሣል..."

1ኛ ሳሙኤል 2:8

37. እግዚአብሔር መንገድህን እንደሚያቀና ተስፋን ሰጥቶሀል።

"እርሱ የቅዱሳኑን እግርይጠብቃል..."

1ኛ ሳሙኤል 2:9

38. እግዚአብሔር እንደሚያበረታህ ተስፋ ሰጥቶሀል።

"ለንጉሡም ኃይል ይሰጣል፤ የመሲሑንም ቀንድ ከፍ ከፍ ያደርጋል።"

1ኛ ሳሙኤል 2:10

# በዳግ ሂዋርድ-ሚልስ የተጻፉ ሌሎች መጽሐፍት

## የታማኝነትና ታማኝ አለመሆን ርዕሶች

- አባቶች እና ታማኝነት
- መሪዎችና ታማኝነት
- ታማኝነት እና ታማኝ አለመሆን
- የሚወነጅሉህ
- ዝንጉዎች
- ትተውህ የሚሄዱ
- አስመሳዮች

## የቤተ ክርስቲያን ግንባታ ርዕሶች

- የቤተ ክርስቲያን እድገት
- ቤተ ክርስቲያን መትከል
- ሜጋ ቤተ ክርስቲያን(2ኛ እትም)

## የመንፈስ ቅዱስ ቅባት ርዕሶች

- ቅባቱን ያዝ
- በምልክቶች እና በድንቆች ማገልገል
- ወደ ቅባቱ የሚያደርሱ እርምጃዎች

## የስኬት ርዕሶች

- አሥራት የማይከፍሉ ክርስቲያኖች ለምን ይደኸያሉ ... እና አሥራት የሚከፍሉ ክርስቲያኖች እንዴት ሀብታም እንደሚሆኑ

## የመጋቢነት አገልግሎት ርዕሶች

- የአመራር ጥበብ 2ኛ እትም
- የእረኝነት ጥበብ
- የመጋቢነት አገልግሎትህን ወደ ላቀ ደረጃ አሳድግ

## የክርስቲያን ሕይወት ርዕሶች

- ወደኋላ ማፈግፈግ
- የጋብቻ ሞዴል
- ልጄ ሆይ፣ ትችያለሽ
- አጋንንቶች እና እንዴት እነርሱን ማሸነፍ እንደሚቻል
- ሰይመው! ይገባኛል በል! ውሰደው!
- የጥሞና ጊዜ
- ንገራቸው!

## የአገልግሎት ሥራ ርዕሶች

- በእግዚአብሔር ፍጹም ፍቃድ ውስጥ መሆን እንዴት እንደሚቻል
- ማጣት፣ መከራ መቀበል፣ መሥዋዕት መሆን፣ መሞት
- የተጠሩ ብዙዎች ናቸው
- ጥሩቶን
- የቤተ ክርስቲያን ሥራ ሕግጋት
- የሙሉ ጊዜ አገልግሎት ሕግጋት